# የዓመፅ ኑዛዜ።



ከአቤ ጉበኛ

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# የዓመፅ ኑዛዜ።

ከአቤ ጉበኛ

መስከረም ፱ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓ.ም ታተመ

እንደገና ነሐሴ ፱ ቀን ፲፱፻፷፪ ዓ.ም ታተመ።

ለማባዛት ወይም ለመተርጐም፤ አስቀድሞ ከደራሲው ካልተፈቀደ በሕግ ክልክል፤ ነው።

ይህ መጽሐፍ መጀመሪያ በ፳፪ኛው የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ዘመነ መንግሥት ታተመ።

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ።

# ማውጫ


መቅድም። ....4
ምዕራፍ ፩። ....6
ምዕራፍ ፪። ....8
ምዕራፍ ፫። ....10
ምዕራፍ ፬። ....13
ምዕራፍ ፭። ....18
ምዕራፍ ፮። ....21
ምዕራፍ ፯። ....27
ምዕራፍ ፰። ....30
ምዕራፍ ፱። ....34
የመጨረሻ ትንፋሼ። ....38
ስለደራሲው በጥቂቱ ....41
Defiance 1975 እ.ኤ.አ. **(በእንግሊ** ....42

# ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት።

«እግዚአብሔርን ምስክር አድርጎ ከራሱ ይልቅ ሀገሩን የሚወድ ነቃፊውን ከምንም አይቆጥረውም።» (ቀ. ኃ. ሥ)

አቤ ጉበኛ።

ሰዎች በሐሰትም ሊወቅሱን ስለሚችሉ ከሰዎች ነቀፋ ነፃ ለመሆን የምናደርገው ጥረት ሁሉ ሙሉ በሙሉ ሊኖረው አይችልም። ኅሊናችን ግን በሐሰት ስለማይወቅሰን በእምነት በእውነትና በቅንነት ብቻ ከኅሊና ወቀሳ ነፃ ልንሆን እንችላለን።

# መቅድም።

ይህች መጽሐፍ በዚህ ቅጽ ለማሳተም ከማሰቤ በፊት በጋዜጣ ማሳተም ጀምሬአት ነበር በዚያ ጊዜ አንባቢዎች በመጽሐፍ ቅጽ እንዳሳትማት ስለተጠየቅሁ በጋዜጣ የመግለጽ ውጥኔን አቋረጥሁና እንደገና በአዲስ መልክ ጻፍኋት። በመጽሐፍዋ የተገለጸው ታሪክ ሰፊና ታላቅ ታሪካዊ ልበ ወለድ ሊሆን የሚችል ነበር። ነገር ግን ብዙዎቹ ደራሲዎችና አንባቢዎች እንደሚያውቁት ታላቅ መጽሐፍ መጻፍ ብዙ ገንዘብ አውጥተው አንድ የአማርኛ መጽሐፍ የመግዛት ልምዳቸው ገና በማደግ ላይ ያለ በመሆኑ ባጭር መንገድ ታሪኩን ለመግለጽና መጽሐፍዋን መጠነኛ አድርጌ በመጠነኛ ዋጋ ለማቅረብ ፈለግሁ።

የእግዚአብሔር ፈቃድ ቢሆንልኝና ዕርዳታው ባይለኝ ምናልባት ወደፊት የሚያስፈልጉትን የሁለትና ሦስት ሰው ንግግሮች (ዲያሎጐች) በሚገባ እየገለጽሁ እጽፈው ይሆናል። ያለዚያም ይኸውም በቂ ሊሆን ይችላል። አንድን ታላቅ ልብ ወለድ ታሪክ ባጭር መግለጽ በሌሎች አገር ጸሐፊዎች የተለመደ ነው። ቀላልና አጭር በሆነ ዘዴ (ሲምፐሊፋይድ እየሆነ) የተጻፈ ብዙ መጽሐፍ አለ።

ይህች መጽሐፌም ቀን ቢያጋጥማት ትልቅ ልብ ወለድ ልትሆን ትችላለች። ባይሆንም የአንድ ራሱን ብቻ ወዳጅ ሰው ታሪክ በኑዛዜ መልክ መግለጿ ለመጽሐፍነቷ ይበቃታል ብዬ አምናለሁ።

ከዚህ ላይ ላንባቢዎች ልገልጽ የምሻው አንድ ነገር አለ። ይኸውም ይህ ታሪክ የአንድ ራሱን ብቻ ወዳጅ ሰው ታሪክ እንጂ የተማረን ወይም ያልተማረን ሰው ለመንቀፍ የተጻፈ አለመሆኑን እያንዳንዱ ሰው እንዲገነዘብልኝ ነው። ባለ ታሪኩ ሰው የተፈጠረው ከተማሩ ሰዎች መካከል በመሆኑ፤ የተማሩትን ሰዎች ሁሉ እንደመንቀፍ ሊቆጠርብኝ አይገባም። ከተማሩ ሰዎች ውስጥ አንዱስ ቢሆን በስኅተቱ ለምን ተነክቶ የተማረ ሊሳሳት ነወይ? ብሎ የሚጠይቀኝ ከመጣብኝ ግን መቼስ እንደፈረደብኝ መልሱን መስጠት አለብኝና «የተማረ ሲያጠፋ ካልተማረ የሚብስበት ጊዜ መኖሩንና ስኅተት ራሱ የተፈጥሮ ጣጣ እንጂ በመማርና ባለመማር ወሰን የተጋረደ አለመሆኑን ማወቅ አለብህ» ብዬ እመልስለታለሁ። ይህን ሁሉ ያናገረኝ ሁሉም ራሱን ንጹሕ ላድርግ ባይ ሌሎችን መንቀፍ እንጂ የራሱን መነቀፍ የማይፈልግ መሆኑን በማወቅ ነው እንጂ አንድ ጸሐፊ ሁልጊዜ ስለመኃይምኖች ስኅተት ብቻ ሲናገር የተማረ በሙሉ ቅዱስ ነው እንዲል ግዳጅ አለበት በማለት አይደለም። አንድ ደራሲ ከማንኛውም ክፍል የደግም ሆነ የክፉ ባለ ታሪክ የመፍጠር መብት አለው።

ከዚህም በቀር ለመንቀፍም ሆነ ለመደገፍ አንድ ሰው ምን ያህል መብት እንዳለው የሚያውቁ ሰዎች እንደዚህ ባለው የአንድ ግላዊ ሰው ታሪክ ውስጥ ገብተው ቢቀየሙ

እንደግፈዋለን የሚሉትን የመንፈስ ነፃነት መቃወም ይሆንባቸዋል። ስለዚህ ማንኛውም ሰው ይህችን መጽሐፍ በቅን መንፈስ እንደሚመለከትልኝና ለምን እንደጻፍኋትም እውነተኛውን ትርጉሟን ይዞ እንደሚረዳልኝ ተስፋ አለኝ።

በመጽሐፍዋ ውስጥም ክፉ *ሥራዎችን* እንጂ በማንኛውም ክፍል ያሉትን ሰዎች እንዳልወቀስሁ ከመጽሐፍዋ የበለጠ ምስክር የሌለኝ መሆኑን አረጋግጣለሁ።

አቤ ጉበኛ።

# ምዕራፍ ፩።

የሞት ጥላ በሕይወቴ ላይ ያንዣብብባታል። በርግጥ ከሞት አፋፍ ላይ ደርሻለሁ። ሞት አሁን እኔን ካለፈ የሚሞት ፍጡር የለም ተብሎ ሊታመን ይችላል።

ለሞት ምቹ ሆኖ የሚገኝ ከተበላቸው የኔ ጤና የበለጠ ምቹ ሜዳ የለም። በእርግጥ ሞት ቀኝ እጇን ይዞኛል። በአልኮልና በዝሙት የደከሙት የደም ሥሮቼ ከዳሁህ ከዳሁህ! ይሉኛል። እጆቼና እግሮቼ እንዳላንቀሳቅሳቸው ከብደውኛል። ይኸው ዝለታቸውም የመገነዛቸው ዋዜማ እንደሆነ ዓመፀኛው ሕሊናዬ በፍርሃት ያስታውሰኛል።

ከፉ ለመናገር እንደ መብረቅ የሚበርቀው አንደበቴ በልጓም ተይዟል። ሦስት ጊዜ ኦፕራሲዮን የሆነው ሆዴ አሁን የመሰናበቻውን ሰንጢ ይጠባበቃል። ዘወትር እያኮፋተርሁ ድሆች ወንድሞቼን የማስፈራራበት ግንባሬ በየደቂቃዎች ከጭንቀትና ከድካም የሚመነጭ ላብ ይጠመቃል።

መልኩ ምን እንደሆነ የማይታወቀው ሞት የተባለ ነገር በፊቴ እየቀረበ ያዝሁህ መጣሁብህ ያለኝ ይመስለኛል። የለበስሁት አንሶላ የተገነዝሁበት አቡጀዲድ እየመሰለኝ ወርውሬ ለመጣል እፈልጋለሁ።

የዛሉት እጆቼ ግን ምኞቴን አላስፈጽምህ ስላሉኝ የጠላሁትን አንሶላ ለብሸዋለሁ። በግራና በቀኝ ታፋዬ የሚነዳድለኝ መርፌ በጐኔ ተኝቼ እንዳልሞት ከመከላከል በቀር አሁን ካለሁበት የሞት አፋፍ ሊመልሰኝ እንደማይችል አውቄዋለሁ።

የደነደነው ሰውነቴ በቀላሉ ባይከሳም የፊቴ ቅርጽ መሰባበርና የቀለሜ መለዋወጥ ግማሽ ሕይወቴ ወደ ሞት ጐዳና እንደተላለፈ ይመሰክራሉ። በእውነት በሞት እጅ ገብቻለሁ።

ከዚህ ወዲህ ዓለምን በበጐ ሥራዬ ልጠቅማት በከፉ ሥራዬ ልጐዳት አልችልም። አሁን ያለችኝ የመጨረሻ ዕድል ሕይወት ያለው ፍጡር ሁሉ ወደ ማይቀርበት ጐዳና የዓለም ብርሃን ተሰናብቼ መጓዝ ብቻ ናት።

ነገር ግን የሚሰማኝ ባገኝ የመጨረሻ ኑዛዜዬን ላድርግ። የሕይወት ታሪኬ እጅግ የከፋ ነው። የነበረኝን ዓቅምና ጉልበት ሳልቆጥብ ለከፉ ተግባሮች አውየዋለሁ። ጉልበት ስላቆጥብ ለከፉ ተግባሮች አውየዋለሁ። ጉልበት ሳገኝ ገንዘብ፤ ገንዘብ ሳገኝ ጉልበት እየቸገረኝ ካለፍኋቸው ነገሮች በቀር በእምነትና በቅን ሐሳብ ተገትቼ ያለፍጓቸው ከፉ ነገሮች አይገኙም።

በዚህ አማላጅ በሌለው ቁርጠኛ ፍርድ ላይ ሁኜ ያለፈውን የሕይወት ዘመኔን ሳስታውስ በዚች ባለችኝ ጥቂት ጊዜ ውስጥ ከፍዬ የማልዘልቀው ከባድ ዕዳ እንዳለብኝ ያስረዳኝ ጀመር።

ከልጅነቴ እስከ ዛሬ የሠራሁትና ያየሁት ነገር ሁሉ ዛሬ ተሰብስቦ በዚች በተኛሁባት ጠባብ ክፍል ውስጥ ይታየኛል። ዓይኖቼ በመጨረሻው ታላቅ ዕንቅልፍ ሊከደኑ ጥቂት ቀርቷቸዋል። ወደ ፊት ለማየት ያደርጉት የነበረውን መቅበዝበዝ የተስፋ መቁረጥ ጨለማ ከልሏቸዋል። አሁን ለማየት የሚችሉት ባለፈው የሕይወት ዘመኔ ሊያዩዋቸው ያልቻሉት ያለፉት ነገሮች ብቻ ነው። ባለፉት ዘመኖቼ ሳላስታውሳቸው ያለፍኋቸው ወይም ንቄ የተውኋቸው ነገሮች ሁሉ አሁን በጸጸት ሰሌዳ ተጽፈው በፊቴ ቀርበዋል። ጽሑፋቸውም በጉልህ ይታየኛል። መልካም ነገሮች እንደነበሩም ከኀዘን ጋር ተረዳኋቸው። እወዳቸውና አሳድዳቸው የነበሩ መጥፎ መጥፎ ነገሮች ሁሉ አሁን ከፊቴ ሸሽተዋል። በሕይወቴ ላይ ከባድ ጥላውንና አስፈሪ ግርማውን በጣለው የሞት ደመና ውስጥ ተሰውረው በሚያስፈረአና በሚያጸጽት ድምፅ ሲያሾከሹኩብኝ ይሰማኛል።

በእርግጥ ሰይጣኖች ክፉ በማሠራታቸው የሚፎከሩ ከሆነ የመጀመሪያው ደረጃ ስላባቸውና መፎከሪያቸው እኔ ነኝ።

ሰው በክፉ ተግባሩ ከሰውነት ውጪ የሚሆን ቢሆን ኑሮ እኔ ከሰው ቀርቶ ከጨካኝ አውሬዎች ጋር ለመቆጠር እንኳ በጭካኔና በብልጠት የሚወዳደረኝ የአውሬ ጓደኛ ባልተገኘልኝ ነበር።

ጨካኝ አራዊት በምን ይነቀፋሉ? ተኩላ በግን እንጂ ወንድሙን የሆነውንና በተፈጥሮ የሚመስለውን ተኩላን አያጠቃም። ክፋውንና የመጨረሻው ተንኰለኛ እባብ እንኳ ሰውንና ሌሎችን ፍጡሮች እንጂ መሰሉ የሆነውን እባብን አድኖ አይነድፍም።

እኔ ግን አድኜ የማጠቃቸው ወገኖቼንና ወንድሞቼን ሰዎችን ነበር። በእርግጥ ዓመፀኛ ነበርሁ እጆቼንና እግሮቼን የተገነዘ ፍጹም በድን በመሰለ ሁኔታ ዘርግቼ እንደታፋዎቼ እምርፌ ባላቆሰለው ጀርባዬ ተንጋልዬ አስፈሪውንና ታላቁን ሞት የተባለውን እንግዳ ሕይወቴን አቅርቤ ለማስተናገድ በምጠባበቅባት በዚች ትንሽ ክፍል ተሰብስቦ የሚታየኝ የዓመፄ ታሪክ ይህ ነበር።

# ምዕራፍ ፩።

እናቴና አባቴ በአንድ የአውራጃ ግዛት ከተማ ጥግ ከከተማው አለፍ ብላ በምትገኝ በአንድ ደማቅ የገጠር መንደር ይኖሩ ነበር።

ወላጆቼ የሚበቃ ሀብት ነበራቸው። በቀበሌውና በአካባቢው በነበሩ ባላገሮች ዘንድ የኔ ወላጆች ተወዳዳሪ የሌላቸው ጌቶች ይባሉ ነበር።

በእውነትም አባቴም እናቴም በየበኩላቸው «አሞራ ዙሮ የማይጨርሰው» እየተባለ የሚሞገስ ሰፋፊ ርስት ነበራቸው።

እኔ በዛሬው ዓይኔ ሳየው አላጋንነው እንጂ በብዙዎቹ ምስኪን ባላገሮች ዘንድ እጅግ ሊሞገስ የሚችል ነበር።

ቆብ ካለ ቦታ ላይ የተሠራው ሰፊ ቤታቸው ግድግዳው በስተውስጥ በኩል ገለባ በጠገበና በቦካ ጭቃ ደኅና ሁኖ የተመረገ ነው።

እጅግም ቋም እጅግም ደሳሳ ሳይሆን አምሮ የተዋቀረውና በቅርብ በቅርብ የተማገረው ባጥ የሸሮ ክክ በመሰለ ንጹሕ ሣር በክፍክፋት ተከድኗል። ዙሪያው ባጋም ሾህ ሽምጥ ታጥሮ በስተ ምሥራቅ ብቻ አንድ በር አለው። በአጥሩ ግቢ ከየርስታችንና ከግል እርሻችን የሚታፈሰው ምርት የሚከማቸው ጐተራዎች የዘላን ጐጆዎች መስለው ይታያሉ። ከአጥሩ ወጣ ብሎ ወደስተቀኝ በኩል የቀንድ ከብቶቻችን የሚያድሩበት ሰፊ በረት አለ። አባቴ የትም ቢሆን፤ ቅርባችን ወደ ሆነው ቤተስኪያን እንኳ ሲወጣ በቅሎ ሳያስጭንና ሁለት ሦስት ባለ ብረቶች ሳያስከትል አይወጣም ነበር።

ማንኛውም የዚያ ቀበሌ ኗሪ፤ እንደሱ ያሉት አንዳንድ ቀንደኞች ካልሆኑ በቀር ሁሉም እርስዎ አንዳንዶቹም «ጌቶች» ይሉት ነበር። በመንገድም ሆነ በሌላ ቦታ የሚያገኙት የቀበሌው ባላገሮች ከሩቅ እጅ እየነሡ፤ በጣም ገራገር የሆኑትም ነጠላቸውን ወይም ጋቢያቸውን እያሸረጡ እጅ በመንሣት ይገናኙት ነበር።

እርሱም የሰላምታቸውን መልስ የሚሰጣቸው ለጠጥ ባለ ቃል «ታዲያስ እንዴት ናችሁ?» በማለት ነበር።

ይህ ዓይነቱን ዕድል ከሰማይ እንደወረደ ልዩ ስጦታ የሚቆጥሩት ባላገሮች በዚህ ሁኔታ እንደ ታላቅ ጌታ ቆጠሩት።

እኔም ብሆን ያንሰዋል አልልም። በዚያ ቀበሌ የሚወዳደሩት አልነበሩም። ከዚህ በላይ ደግሞ በልጅ በኩል የነበረው ዕድል የሚያስቀና ነበር። እናታችን በላይ በላዩ መንታ

መንታውን ትውልድ ነበረች። በሀብት የሞቀው የወላጆቼ ቤት ያለደመወዝ የሚያገለግሉ ገረዶችና አሽከሮች የሚተራመሱበት ከመሆኑ በላይ በየሁለት ዓመቱ መንታ መንታ ሕፃናት ለአባታችን ማበርከት ልማዷ የሆነችው «ሽለሙቅ» እናታችን ባፈራችን ሕፃናት ደምቆ ይታይ ነበር። የናቴ ዓይነቱ አወላለድ በደሀ ቤተ ሰቦች ላይ ቢደርስ እጅግ አሳዛኝ ነገር ነው። ሁለትና ሦስት ሕፃናት ለማሳደግ ዓቅም የሌላቸው ድሆች የአሥርና የአሥራ አምስት ሕፃናት ጌቶች ሁነው፤ ግማሹ ደስ የምትል የሕፃን ሆዱን ራቁቷን ዝርኩት አድርጎ ተንቦሽ ተንቦሽ ሲል፤ ግማሹም የሕፃንነት ወበቱን አመዱና አቧራው አጥፍቶት ወንተር ወንተር ሲል ማየት በእርግጥ የሚያሳዝን ነገር ነው። በኛ ቤተ ሰብ ውስጥ ግን የሕፃናት መበርከት ተጨማሪ ደስታን ቸገረን ብለው ያስቡ? እህሉ ከጐተራቸው እንዳፈር ይዛቃል። ቅቤውና ወተቱ ከላሞቻቸው ይገኛል። ገረድና አሽከር በነፃ ይሠራል። ስላሽከሮችና ገረዶች ኑሮ «ጠዋትና ማታ አንዳንድ ወፍራም የገብስ እንጀራ በባቄላ ሽሮ ይልፋል፤ በዓመት ለሴቶች አንዳንድ አቦጀዲድ ቀሚስ፤ ለወንዶች አንዳንድ የአቦጀዲድ ጋቢ ከጥብቆውና ከቁምጣው ጋር ይሰጣቸዋል፤ አነሰ? አኾኾ! በጣም የሚያመሰግን እንጂ ምን ያንሳል!!» የሚለውም ብዙ ነበር።

ሁሉም ሙሉ ነበር። ሕፃናትን የሚያስጠላው ችግር በአጥረ ገጣችን አይደርስም ነበር። ታዲያ ምን ይሆናል? የዚህ ዓለም ጣጣና ችግር ባላሰቡት መንገድ መጥቶ ነው በጉድ የሚያወጣ። በአካባቢያችን ያሉ ባላገሮች አባቴ ከፍጹም ደስታ የደረሰ ኀዘንም የማይነካው ሲመስላቸው፤ የነበረውን እንዳልነበረ የሚያደርገው ድንገተኛ ሞት ባልታሰበበት መንገድ መጥቶ ጉድ ሠራን። በጥቢ ወራት ላይ እንደ ተስቦ ያለ ወረርሽኝ መሳይ መጥቶ ከሁለት ሳምንት በማያንስ ጊዜ ውስጥ እናቴንም አባቴንም ቅንጥስ! ቅንጥስ! አድርጓቸው ሔደ።

እናቴ በዚያ ጊዜ ታጠባው የነበረ ዕድለኛ ሕፃን ከእናት ከአባቱ ጋር ዕዳውን ጠቅሎ አብሮ ከመሔዱ በቀር ከልጆችም ሆነ ከአሽከርና ከገረድ አንድም አልተነካ። ግን መኖር አይበለው! ትርፉ አሣር ነው።

ከቀሩት ወንድሞቼና እኅቶቼ ይልቅ ከኔ እንኳ ሳይቀር ከእናቴና ከአባቴ ጋር የሞተው ሕፃን በጣም የታደለ ነው። እናታችንና አባታችን በአንድ ሰሞን ሲሞቱ ታላቁ ቤተ ሰባችን ፈጽሞ ተናደ፤ ሁሉም ነገር አለፈ።

እኔ ይህን ያህል ልጅ ይዣለሁ እያሉ ከወላጆቻችን ብዙ ሀብት የሚበልጠውን ክፍል ለመሳተፍ የተቀናኑ አክስቶቻችንና አጎቶቻችን እኔ እወስድ! እኔ እወስድ! ሲሰላለፉብን የተመለከተ እንዴት ያሉ መልካም ቤተ ዘመዶች ናቸው? እግዜር ይባርካቸው እንዲህ ያሉ ዘመዶች ካሉ ቢሞቱስ ምን አለ!! ብሎ ይደነቅ ነበር።

ግን ከኔ የማይሻሉ ፍጹም አውሬዎች ናቸው እርግጥ ነው፤ የዛሬው እኔ ከሰው ቀርቶ ከአውሬ የምከፋ መሆኔን አምናለሁ። ከኔ ቤተ ዘመዶች የበለጠ የምከፋ አውሬ ነኝ ለማለት ግን አልችልም። እነሱም እኔም ያው ሰይጣኖች ነን።

# ምዕራፍ ፫።

የናት አባታችንን ንብረት ጠብቀን ራሳችንን ለመርዳት በማንችልበት ጊዜ ሁለቱንም ወላጆቻችንን ያጣን ሕፃናት ተከፋፍለን መኖር ግድ ሆነብን። የእኛን ዝምድና ሳይሆን የወላጆቻችንን ጥሪት የፈለጉ ቤተ ዘመዶች እንደ ቅርጫ ሥጋ በዕጣ ተካፈሉን። እንደ አጋጣሚ እኔና የመጨረሻዋ ትንሽ ማለት ከነ እማማ ጋር ከሞተው ሕፃን ቀድማ የተወለደችው እኅቴ ከአንድ አጐታችን ቤት ገብተን ነበር። ወደዚህ ቤት ከተመራን ሳምንት እንኳ ሳይሞላን ያጎቴ ሚስት ከፍ ያለ የጭካኔ ሥራ ስትሠራ አየኋት። ትንሿ ሕፃን እህቴ አንድ ቀን ጠዋት ሴትዮዋ ወጥ ስትሠራ ክክ አየችና ተንከር ተንከር እያለች ሂዳ ከፊቷ ቁማ «እማማ! ክክ!» አለቻት።

«ያልወለደ አረደ» ይገርማል! ትንሿን ሕፃን ገና እንስሳዋን እንደኔ እንኳ ተናግራ የማታስቀይመውን ለጋ ሕፃን «ወግጅ ከፊቴ ኧረ ይህች ባለጌ!» አለቻት። ሕፃኗ ግን የድምጹ ቃል ቁጣ መሆኑ ቢታወቃትም «ወግጅ ከፊቴ ኧረ ይችህ ባለጌ» የሚባለው የመረረ ኃይለ ቃል ስምታው የማታውቀው፤ አማርኛው የማይገባት ስለነበረ መልካም የተናገረችላት መስሏት ሁለቱን ትንንሽ እጆቿን በአንድ ላይ ግጥም አድርጋ ወደራሷ አወጣችና ወደ ሴትዮዋ እያስተዋለች «እህህ» ብላ በመካከላቸው ፍንጪት ያሉባቸው ለጋ ጥርሶቿን ብልጭ አደረገች። ወይ ፍንክች የማን አንጀት ነው ለሰው ዲቃላ የሚራራ። «ኧኸ እንዲች ነኝና ስድ አደግ ልጅ ካልቆነጠጡት መቼ እሺ ይላል!» ብላ ያንጠውሌ ክንዷን ወደ ሕፃኗ ጭን ዘርጋ አድርጋ ባልተወለደ አንጀቷ እርም አደረገቻት። ይገርማል! በኃይል እንደ መዘለገቻት እነዚያ የጉጉት ዓይኖች የመሰሉ ዓይኖቿ ከጐራዳውና ከድፋንፉኑ አፍን ጫዋ በላይ የስሙኒ ሞፎ መስሎ በሚታየው ጉንጭዋ እስኪሠውሩብኝ ድረስ ፊቷ ጭምድድ ግን ባሯ ኩፍትር ሲል በማዬቴ ተረዳሁ። ጧት ከጭኗ ሳይነሳ ሕፃኗ ወደ ኋላዋ ሸሸት ስትል ስለለቀቀቻት እግዚአብሔር የረገማት ሕፃና ከደረቁ የአፈር ወለል ላይ በጀርባዋ ተዘርራ ከእሳት እንደገባች እርር ትክን እያለች ትጮህ ጀመረች። የመጀመሪያ ልጅ የምትባለው እኔ የ፲ ዓመት ልጅ ስለነበርሁ በዚች በትንሽ ሕፃን እኅቴ ላይ የተደረገው ቅጣት ፍጹም ወንጀል መሆኑ ከንዴት ጋር ገባኝ። ተቀምጬበት ከነበረው መደብ ብድግ ብዬ «ምን አደረገችሽ? ኧረ ምን ያለችው ክፉ ሴትዮ ናት!» አልሁና ሕፃኗ ከወደቀችበት ሂጄ ቀና ሳደርጋት ከተቀመጠችበት ብድግ ብላ ቀኝ ክንዴን ያዘችኝና «ኧረ ይኸ ያልታረመ

ስድ አደግ የባለጌ ልጅ ሁሉ። ደግሞ ሊሰድበኝ ነው» ብላ በባልዋ ክንድ ሁለት በሚሆነው መረመንጅ ክንዱ ጆሮ ጥላዬን በጥፊ ላገነችኝ። «እንዴ!! ምን አደረግንሽ?» አልኋት።

«ደግሞ ይመልስልኛል!» አለችና ጆሮዬን ይዛ ያንን የሚቀናትን የቁንጥጫ መዓት አወረደችብኝ። ጆሮዬን ጥቂት ካፍተለተለችኝ በኋላ ወደ ላይ ሳብ ስታደርገው ከመባቀያው ላይ ቆዳው ጥቂት ቀርደድ ብሎ ደም ችፍፍ አለበት። ጆሮዬን ለቀቀችና ጭኔን ይዛ አንድ ጊዜ እንደመዘገችኝ እንደምንም ብዬ ከጅዋ አምልጬ ወደ ውጭ ሮጥሁ። ወጥ ታማስልበት የነበረውን የእንጨት ማንካ ይዛ ከበሩ ድረስ እየሮጠች ተከትላ ማንካውን በዚያ ጠብደል ክንዱ ብታምዘገዝገው ማጅራቴን ጠቅሎ ሊጥለኝ እግዜር አወጣኝ። የተምዘገዘገው ማንካ በጆሮ ጥላዬ «እሩሩሩ» የሚል ነፋሳዊ ድምፅ አሰምቶ ሲያልፍ ጨካኝነቷን ደኅና አድርጎ ስላስረዳኝ ከዚች ሴትዮ ጋር አብሬ ለመኖር የነበረኝን ተስፋ ለመቁረጥ በቂ ምክንያት ሆነኝ።

ራሳቸውን ላልቻሉት ሕፃናት ይብላኝ እንጂ እኔስ እንግዲህ ራሴን አልጥለውም የናት አባቴን ነፍስ ይማር! አስተማሪ ቀጥረው ዳዊት አስደግመውኛል ንባብና ጽሕፈት አስተምረውኛል። ዕድሜዬ ፲፬ ዓእምት አልፎ ፲፭ኛው ጀምሯል። በምቾት ያደገው አካሌም ከዚህ በላይ የበለጠ ዕድሜ አለው ተብዬ ለመገመት አድርሶኛል።

እግዜር ባይልልኝ ነው እንጂ አባባና እማማ ቢኖሩ ሚስት ማጠያየቃቸው የማይቀር ነበር። ታዲያ በምን ምክንያት ነው በዚች አውሬ እጅ የምሠቃየው? ከአጐቴ ቤት ራቅ ካለ ቦታ ላይ ሁኜ ይኸንና ይኸን የመሳሰለውን ሐሳብ ሳሰላስል ከቆየሁ በኋላ «ወዴትአባትህ ትገባለህ? መድረሻቢስ መሆንህ ጠፋህ? የአባት እናትህን ቤት እስኪ ሂደህ ተመልከተው። ያ ደማቃ ግቢ ወፍ እንኳ የማይዞርበት ምድረ-በዳ ሁኗል። የአባትህና የናትህ ሀብት በስንት ሰዎች እጅ ገብቷል። ዛሬ ያንተ መጠጊያ የት ነው?» የሚል ድምፅ በኅሊናዬ ጆሮ እየቀረበ ይጮህብኝ ጀመር። በአንድ በኩል ደግሞ «ዛሬ እንደ አንተ ያለ ልጅ በሚገባ ለመማር ሲችል የናት አባቱን ሀብት በቤተ ዘመዶቹ እጅ እየተመጸወተ የዕለት ጉርሻውን ማግኘቱ እንደብዙ ነገር ተቆጥሮበት ርኅራኄ በሌላት አንዲት ክፉ ሴት እጅ እየተነረተ ለምን ይኖራል? ሂድና ትምህርትህን ቀጥል» የሚል፤ ስሜት መጣብኝ። በሁለቱ ሐሳቦች ላይ የኅሊናዬን ፍርድ ካመላለስሁ በኋላ በሁለተኛው ሐሳቤ ተስማማሁ።

ወዲያው ወደ አውራጃዋ ግዛት ከተማ መንገዴን ቀጠልሁ። ወደ ከተማዋ ለመሄድ ስነሣ መጀመሪያ ሞት ወዳፈረሰው የወላጆቼ ቤት ሄድሁ። ከአጥሩ ጥቂት ራቅ ብዬ እየዞርሁ የቤቱንና የአጥር ግቢውን ሁኔታ ስመለከት እናቴና አባቴ በሞቱባቸው ቀኖች ከተሰማኝ ኀዘን ዕጥፍ የሚሆን ከባድ ኀዘን ተሰማኝ። አጥሩን ከመቼው ማፍረስ ጀመሩት!! ሣሩ ከመቼው ገንግኖ ግቢውን ወረሰው ቤቱ ከመቼው እንደዚህ ተጐሳቆለ!! የከብቶችን

በረት ከመቸው አፍርሰው ወሰዱት። አቤት ብልጠጥ! ነገ ለሁሉም በየተራው ይደርሰዋል። እያልሁ በአጥሩ ዙሪያ ስንከራተት በአንድ በኩል አጥሩ በጣም ፈርሶ አገኘሁት። በተቀደደውም አጥር የቤቱ በር በኋሊት እንደተዘጋ የአጥሩን ግቢ ጨምሬ አየሁት። አባቴ ከውጭ ቆይቶ ሲመጣ ድምጹን ስሰማ እበር ወጥቼ አባባ ብዬ ጉለብቱን ስስመው አንገቴን ቀና አድርጎ ዝቅ ብሎ ጉንጮቼን ይስምበት የነበረው፤ ከልጆች ጋር ስንጫወት ቆይቼ ወደ ቤት ስመለስ እናቴ ከወንበር ላይ ቁጭ ብላ ትንንሾችን እኅቶቼንና ወንድሞቼን ስታጫውት አግኝቼ «እማምዬ» ብዬ አንገቷን ጥምጥም አድርጌ ስይዛት ጉንጬን አገላብጣ ትስምበት የነበረው ቦታ ሁሉ ፍጹም ባዶ ሁኖ ታዬኝ ይህን አሰቃቂ ሁኔታ የእንባ መንጠላእት በጋረደው ዓይኔ ስመለከት፤ «ከጠፍ ምድረ በዳ ላይ ምን አቁሞሃል? የዚህ ቤት ሞገስ የነበሩት እናት አባትህ አፈር ሁነውልሀል! የሞት ሥራ ይኸውልህ ይኸን መሳይ ነው!! እዚህ እናትህ የለችም አባትህም የለም!! ከአሽከሮቻችሁና ከገረዶቻችሁ አንዳቸው እንኳ የሉም!! ያንተ እዚህ ቤት ማደግ በቃህ!!» የሚል መንፈስ ድምፅ ተሰማኝ። አዲስ መርዶ መጥቶ አካሌን አደነዘዘው ሰውነቴንም አዲስ ኀዘን ዋጠው ድንገት «እማምዬ! ወይ አባት ዓለሜ ኧረ ከምን ልድረስላችሁ!!» አልሁና ራሴን በሁለት እጄ ይዤ እጮህ ጀመር። ከዚያም ከአጥሩ ጥቂት እራቅ ብዬ ቁሜ ተስፋ በቆረጡ ዓይኖቼ «የሟች ቤት» የሚል ምልክት በሁኔታው ገልጾ የሚያሳየውን የጥንት ቤታችንን እየተመለከትሁ ስንሰቀሰቅና ስቀጠቀጥ ቤቸኛ ከነበረው ቤታችን ጥግ ካሉት ቤቶች የአንዱ ባለቤት የሆኑት ሴትዮ አይተውኝ ኑሮ ከቤት ተነሥተው ከሳ ባሉት ጉንጮቻቸው እንባቸውን እያፈሰሱ መጡና «የኔ አባት እንግዲህ ለምን ይሁን ብለህ ነው? ከዛሬው ምን አስቀይመውህ ይሆን?» እያሉ ወደኔ ቀረብ አሉ።

እኔ ግን ዝም ብዬ እንሰቀሰቅ ነበር። አዛኟና ርኅርሂቷ ሴትዮ ምንም እንኳ የርሳቸው እንባም እንደኔው አስቸግሮ አልገታ ቢላቸው በአንድ እጃቸው አንገቴን ይዘው በአንድ እጃቸው ንጹሑን ኩታቸውን በዘርፉ በኩል ይዘወ እንባዬን ጠራረጉት። የርሳቸውንም እንባ እንደዚሁ በኩታቸው ጠረጉና በል ወደ ቤት እንሂድ ብለው ወደ ቤታቸው ወሰዱኝ።

እቤት እንደደረስን እንደ ልጅ ሳይሆን እንደ ታላቅ ሰው በከበሬታ አስቀምጠውኝ፤ እንደ ሌሎች፤ ልጅ ወይም ሌላ ሰው ሳይልኩ፤ ኩታቸውን ከትከሻቸው ወረድ አድርገው አስቀምጠው ጓዳና ማጀት አሉና የምበላውን የምጠጣውን ከመጠኔ በላይ አቀረቡልኝ። ያቀረቡልኝ ምግብ እናቴ ከሞተች እስከዚያ ድረስ ቀምሸው የማላውቅ ጥሩ ምግብ ነው።

የጠራውን ጠላ በማንቆርቆሪያ አቀረቡልኝ ትንሽ ቆየት ብለው «አዬ አፈር በበላሁ። ወተት እኮ በጣም ትወድ ነበር!» ብለው ከተቀመጡበት ተነሡና ወተቱንም በታላቅ ብርጭቆ ቀድተው ሰጡኝ። ያቺን ጨካኝ ሴት በጠዋቱ ለከፋኝ ያውን የሕይወት ማንቀሳቀሻ የሆነ ቁራሽ እንኳ ሳላገኝ ባዶ አፌን ወጥቼ በጣም ተርቤ ስለ ነበር መልካሟ

ሴትዮ ያቀረቡልኝን ምግብ ቶሎ ቶሎ ጐርስ ጐረስ እያደረግሁ እባላ ጀመር። እንደ እናቴ የብዙ ልጆች እናት የሆኑት ደግ ሴትዮ በረኀብ መጐዳቴንና በባዶ ጠቀርሻ ጥግ ቁሜ በሚያሳዝን ድምፅ መጮሄን በማየታቸው ልባቸው በጥልቅ ኀዘን ስለ ተወጋ እኔ እልቅሶዬን አቋርጬ ያቀረቡልኝን ምግብ ስበላ፤ እርሳቸው እኔን እኔን እየተመለከቱ እንባቸውን ያፈስሱ ነበር።

እኒህ ሴትዮ ለእአናቴ ልዩ ወዳጅና መልካም የባዕድ ጐረቤት የነበሩ ናቸው። እናት አባቴ ሲሞቱ ያንጀት እንባ አልቅሰው ከቀበሩዋቸው እውነተኞች ወዳጆች መካከል አንዷ ናቸው። እንደ እኔ እናት «የብዙ ልጆች እናት ናቸውና እግዚአብሔር ዕድሜውን መጽውቶ የልጆቻቸው እናት ያድርጋቸው» የሚል ምኞት ነበረኝ።

# ምዕራፍ ፬።

ከቀረበልኝ ምግብ ሆዴ የቻለልኝን ያህል በላሁ። ወተቱን ጠጣሁ። ከጠላውም ቀማመስሁ። ከዚህ በኋላ ተነሣሁና ልሂድ አልሁ። ሴትዮዋም «እንዴ! ቆይና አድረህ ነው የምትሄድ ወንድሞችህ (ልጆቻቸው) ሲመጡ ከነሱ ጋር ስትጫወት አድረህ ነገ ትሄዳለህ» አሉኝ።

«የለም እሄዳለሁ እማማ ወላንሣ።» አልኋቸው «ብትሄድም ቆይ ጠሐዩ ይብረድልህ» አሉኝ። ንግግራቸውን ለሰማና እኔን የሚያዩበትን ዓይናቸውን ላስተዋለ ሰው በእርግጥ ርኅራኄ ያላቸው እውነተኛ የልጆች እናት ኢትዮጵያዊት መሆናቸውን ያስረዳ ነበር። የምቸኩልበትን ጉዳይ ሲጠይቁኝ የምሄደው ወደ አጐቴ ቤት ሳይሆን ወደ አውራጃዋ ግዛት ከተማ ሂጄ ትምህርት ቤት የምገባ መሆኔን ነገርኋቸው።

«ከየትኛው ተማሪ ቤት ልትገባ ነው?» ሲሉ እማማ ወላንሣ ጠየቁኝ።

«ከመንግሥት ተማሪ ቤት» አልኋቸው።

«ከአስኳላው ነው?» ሲሉ ደግመው ጠየቁኝ። «አዎ!» አልኋቸው።

«እሺ መልካም ነው። እግዚአብሔር እንዳመለከተህ ሂድ፡ ግን አሁን ቆይና ወንዶች ሲመጡ ባለቤቴ ወይም ወንድምህ ትልቁ ልጄ ወስደው ያደርሱሃል። ከከተማው የኔም የባለቤቴም ዘመዶችና ወዳጆች ስላሉ ሌላው እንኳ ቢቀር መጠጊያ እንዲሆኑህ ከነሱ አገናኝተውህ ይመለሳሉ። ከዚህ ካሉት ዘመዶችህም ቀለብህን በየጊዜው እንዲልኩልህ ይነግሩልኻል።» በማለት የተፈጥሮ ርኅራኄ የታደሉት ወይዘሮ ወላንሣ መከሩኝ።

እኒህ መልካሚቱ የናቴ ጓደኛ ይህን መንገዴን የሚያቀና ምክር ሲመክሩኝ ምንም ልጅ ብሆን፤ በመልካም ሁኔታ ተረዳሁት።

ምክራቸውን እሺ ብዬ ከተቀበልሁ በኋላ ወደዚያ ጊዜ የከዳው ጠቀርሻ ሂጄ እንዳላለቅስ በመሥጋት አንድ ጊዜ ቆሎውን አንድ ጊዜ ንፍሮውን አንድ ጊዜ እንጀራውን እያቀረቡ ሲያባብሉኝ ከቤት ሳልወጣ ጊዜው መሸ። ማምሻ የቤቱ ባለቤት አቶ ውብነህ ከልጆቻቸው ጋር ከዋሉበት የገብስ አጨዳ ሥራ ተመልሰው መጡ። ለጥቂት ጊዜ ራቅ ወዳለ መንደር ሂጄ የቆየሁትን ልጅ ከቤታቸው ቁጭ ብዬ ሲያዩኝ አባትዮውም ወጣቶች ልጆቻቸውም ያሳዩኝ ፈገግታና የፍቅር ስሜት እንደኔ ላለው ውለታ ቢስ አይታሰበው እንጂ ቅን መንፈስ ለታደሉት ሰዎች ምን ጊዜም የሚረሣ አልነበረም። ሁሎችም በናፍቆት ጉንጩን እያገላበጡ ስመውኛል። በነዚህ ደግ ጐረቤቶች ቤት ያሳለፍሁት ቀንና ሌሊት፤ ከናት ካባቴ ቤት ከኖርሁባቸው ቀኖች የሚያንስበት ነገር የለውም። ይሁንና ይህ ሁሉ ሲደረግልኝ ወላጆቻቸውን ባጡ ልጆች ላይ የሚታየው የመፍዘዝ የቅርታ ስሜት በግንባሬ ላይ ይነበብ ነበር። ሲስቁ አልስቅም። አንዳንድ ነገር ጠይቀው ሲያነጋግሩኝ እናገራለሁ እንጂ ሌላ ቃል አልተነፍስም። ያ ሁሉ ሲሆን ዓይኖቼ ወደ መሬት እንዳቀረቀሩ ማንንም ቀና ብዬ ሳላይ ተቀምጬ ነበር። ልጆችም ወላጆችም በልቤ የተቋጠረውን የኀዘን እረመጥ ለጊዜው ገብ ለማድረግ ለማጫወትም ለማሳቅም ሞክረው ነበር። ነገር ግን እንዴት ሁኖ? ግንዴ ብቻ እዚህ ቤት ተቀምጧል እንጂ ኅሊናዬ ወዲያና ወዲህ ይመላለሳል። እናት አባቴ ሳሉ የነበረውን የቤታችንን ሁኔታ አስቤ አሁን እኅቶቼና ወንድሞቼ ከነማን እጅ እንዳሉ። ቤታችን ምን መስሎ እንዳየሁት፤ ከአጐቴ ቤት በወጣሁ ጊዜ በሕጻኗ እኅቴ ላይ ምን ሲደረግ እንዳየሁ እይሰላሰልሁ በብረት ድስት እንደ ሚፈላ ውሀ እየገነፈለ የሚተናነቀኝ እንባ በይሉኝታ እየተቆጣጠርሁ ተቀምጫለሁ። በዚህ ሁኔታ ከመልካሞቹ ጐረቤቶች ቤት አምሽቼ ደኅና መኝታም ተሰጥቶኝ አደርሁ። ወይዘሮ ወላንሣ ማታውን የኔን ሐሳብ ለባለቤታቸው ለአቶ ውብነህ ነግረዋቸው ኑሮ በጠዋት ተነሥተው ከደንበኛ ምሳ የሚበልጥ ቁርስ አዘጋጅተው አበሉንና አቶ ውብነህ ልጆቻቸውን ወደ ሥራ ሸኝተው እኔን ወደ ከተማዋ ለማድረስ የአደባባይ ልብሳቸውን ለባብሰው ተነሡ። ወይዘሮ ወላንሣም በሁለቱ ዓይኖቻቸው የተንቸረፈፉ የዕንባ ጤዛዎችን በመዳፋቸው ጀርባ ጠራርገው ጉንጮቼን ስመው ተሰናበቱኝ። አቶ ውብነህ ፊት ለፊት ሁነው ሲጓዙ በሁለት ትከሻቸው ላይ እንደ በሬ ቀንበር አጋድመው የያዟትን ከዘራቸውን ከላይ አይቼ ከታች ደግሞ ከቋንጃቸው ጥቂት ወረድ ብሎ ቀጭን ረጂም ሱሪያቸውን ያለበሰውን፤ ኩታ የተደረበበት እጄ ጠባብ እያስተዋልሁ በእግር በእግራቸው መከተል እንደጀመርሁ ድንገት ወደ መንደሩ ዘወር አልሁ።

ሞት የፈታው ቤታችንም በቅርቡ ግትር ብሎ ታየኝ። ዓይኔን ከቤቱ ሳልመልሰው እንባዬ እርግፍ እርግፍ ማለት ጀመረ። አቶ ውብህን ኮቲዬ ሲጠፋባቸው ጊዜ ዘወር በለው ቢመለከቱኝ በእንባ ስታነቅ አገኙኝ። «እሳቸውም ወደኔ መለስ ብለው በቀስታ ራመድ ራመድ እያሉ «ምን ሆንህ የኔ አባት? መቅረት ፈለግህ!?» አሉኝ። እኔ ምንም አልመለስሁ። አንገቴን እንደደፋሁ ስቅ ስቅ ብዬ አለቅሳለሁ። ከትከሻቸው ላይ የነበረውን ከዘራ ወረድ አድርገው በቀኝ እጃቸው ከመሬት ላይ ቆም አድርገው ወገባቸውን በከዘራዋ ጫፍ ደገፍ አድርገው እኔን በኀዘን እየተመለከቱ ቆም አሉ።

ወዲያው «ለመሄድ አትፈልግ እንደሆነ አታስብ ግድ የለህም። ዘመዶችህ አንገላተውህ እንደሆነም ከኛ ጋር ትቀመጣለህ። ከልጆቼ በምንም አልለይህም የኛ ቤትም እንዳባትህ ቤት አንድ ቀን የሚፈታ ነው። በምንም ቅር አይበልህ ዘመድ በማጣት ወደ ማትፈልገው ቦታ መሄድ የለብህም። እኛም እንደ ወላጆችህ ስንሆን በግድ ትሄዳለህ አሉኝ። እኔ ግን መለስ አድርጌ «የለም ለመማር እፈልጋለሁ።!!» አልኳቸው።

«እኔም እኮ ትምህርት መፈለግህን አልጠላሁም እንደዚህ የምልህ ምናልባት፤ በኑሮህ ተበሳጭተህ ከአገር ለመጥፋት አስበህ ያደረግኸው እንዳይሆን ብዬ ነው» ሲሉ ከጊዜ ጋር የማይከዱት የአባቴ ጓደኛ ነገሩኝ። «የለም እነ አባባም ባይሞቱ በትምህርቴ ለመግፋት ማሰቤ አይቀርም ነበር» ስል መለስኩላቸው። «ታዲያ አሁን ለምን ታለቅሳለህ» አሉኝ።

ምንም አልመለስሁ። «ልጄ መቸስ የምትፈልገውን ንገረኝና በሚቻለኝ ልርዳህ እንጂ እኔንስ ለምን ታስጨንቀኛለህ?» በማለት ተናገሩ። ዓይኖቻቸውን በኔ ላይ እንዳሳረፉ ቀና ብዬ ባያቸው ደፍረስ ብለው የሚታዩ ትልልቅ ዓይኖቻቸው የርኅራሄ እንባ ቋርዘዝ አድርገዋል። በዚህ ጊዜ ሰውን ጨምሬ በኀዘን ማንገላታት ተሰማኝ። የሞቱት ወላጆቼ አምላክ የሰጠኝን እውነተኛ ዘመዶች በሰቀቀን ማሰልቸት እንደማይገባኝ ተረዳሁ። በዚህ ጊዜም «እሺ መንገዳችንን እንቀጥል አባባ ውብነህ» አልኳቸው።

«ለመሆኑ አህን ምን ትዝ ብሎህ ነው ያለቀስህ?» ሲሉ ልባቸውን የከነከናቸውን ነገር ለመረዳት ጠየቁኝ።

«ቤታችንን ሳየው ጊዜ ነው።» አልኳቸው። አባቴንና እናቴን በሚገባ አልቅሰው የቀበሩት ደጉ ጐረቤት እንደ አዛኟ ባለቤታቸው እርሳቸውም አዛኝ ስለ ነበሩ በዓይኖቻቸው የተቋጠረውን ዕንባ በጉንጫቸው አወረዱት። በእርግጥ ከአንጀታቸው አለቀሱ። አንድ ወንድ እንደዚህ ባለው የርኅራሄ ስሜት ፍጹም የሆነ ዕንባ ሲያፈስ በሕይወቴ ሙሉ ያየሁት አቶ ውብነህ ለኔ ራርተው ባለቀሱበት ቀን ብቻ ነው። በየአክስቱና አጐቱ ቤት ወድቀው የሚንገላቱት እኅቶቼንና ወንድሞቼን ቢያዩ ሁልጊዜ ሲያልቅሱ እንደሚኖሩ ርኅራኄያቸው ገልጾልኛል።

አቶ ውብነህ ዕንባቸውን ከጠራረጉ በኋላ እኔን ፊት ለፊት አድርገው መንገዳችንን ቀጠልን። ቦታው ቅርብ ስለ ነበረ ወደምንሔድበት ከተማ ሰባት ሰዓት ተኩል ግድም ላይ ደረስን። እከተማዋ በደረስን ጊዜ በዘመኑ እንደ ብርቅ ይታዩ የነበሩትን አንዳንድ ኖራ የተቀቡና ቆርቆሮ የተከደኑ ቤቶች ሳይ አንድ አዲስ ስሜት ተፈጠረብኝ። በከተማዋ መካከል ውር ውር የሚለው ሰው ስመለከት አቶ ውብነህንም አቁሜ እስከ ማስጠበቅ ደርሼ ኔብር ያን ጊዜ ዕፁብ ድንቅ ሁና በታየችኝ በዚች ትንሽ ከተማ የማየው ነገር ሁሉ ተለወጠብኝ። ቤቶቹ አብዛኛዎቹ በኛ መንደር መሰላቸውን አይቼ የማላውቅ ናቸው። ሰዎቹ የለበሱት ልብስ ተወልጄ እስከዚች ቀን በቆየሁባት መንደር ያሉ ባላገሮች ከሚለብሱት እጅግ የተለየና በዚያ ጊዜ ፍጹም ዕንቊ መስሎ የታየኝ ነው።

አባቴ እንኳ በቀበሌው ታላቅ ጌታ ተብሎ ሲኖር በአለባበሱም ሲደነቅለት ከነዚህ ከተሜዎች ከተራው ሰው እንኳ የሚወዳደር ልብስ ለብሶ አይቸው አላውቅም። ብዙዎቹ ወንዶችና ሴቶች በጥሩ ጥሩ ጫማ ይሔዳሉ። ብዙ ቆንጆ ቆንጆ ሴቶች አያለሁ። የለበሱት ልብስ እማማ ትለብሳቸው ከነበሩት ጥልፍ ቀሚሶችና ዕጥፍ ኩታዎች የተለየ ነው። አካሔዳቸውም አለባበሳቸውም አነጋገራቸውም ዕንግዳ ሆነብኝ። ይህን ሁሉ እየተመለከትሁ ስሔድ በየቦታው ዕንቅፋት ያጤሰኝ ነበር። አቶ ውብሀን «አሁን ትጠግበዋለህ ቶሎ ላድርስህና ልመለስ ብዙ ሥራ ትቼ ነው የመጣሁ» እያሉ ባይጎሰጉሱኝ ቀኗን ሙሉ እገበያዋ መኻል ቁጭ ብዬ ባሳለፍኳት ነበር።

በዚህ ሁኔታ ስንጓዝ ወደምንሔድበት የአቶ ውብነህ ዘመድ ቤት የምትወስደውን ቀጭን መንገድ ይዘን ሰፊውን ጐዳና ለቀቅ እንዳደረግን አንድ ትሬንታ ኳትሮ እያጓራ ሲመጣ ወደ መንፈዱ ዘወር ብል እንደ ጉድ ሆኖ ታየኝ። ጥቂት ጥቂት ዘወር ብል እንደ ጉድ ሆኖ ታየኝ። ጥቂት ጥቂት እንደ ፍርሃት እየሞከረኝና ወደሳቸው ቀረብ እያልሁ «አባባ ውብነህ አባባ ውብነህ! ይህ ነገር ምንድን ነው?» አልኋቸው።

«እስከ ዛሬ ወደ ከተማ መጥተህ አታውቅም?» አሉኝ።

«ኧረ መጥቼም አላውቅ። ይህ አሁን በዚህ መንገድ ያለፈው ጭዋሂ- ነገር ምን ይባላል? ርቡላ ነው? ርቡላ ደግሞ በሰማይ ነው የሚበረው» አልሁ።

«የለም ይኸ ካሚዎን የሚባል መኪና ነው። መኪናውንም አውሮብላኑንም አይተህ ትጠግበዋለህ አሁን እንሒድ» አሉኝ። ከተወለዱባት መንደር ወጥተው የማያውቁ ባላገሮች እንደዚህ ለወጥ ያለ ነገር ባዩ ቁጥር በትንሹም በትልቁም መገረማቸው የታወቀ ነው። ምናልባት እንደኔ በገጠር ተወልዳችሁ ያደጋችሁና በኋላ ከተማ ያያችሁ በገለጽሁላችሁ ታሪክ ሳታምኑ አትቀሩም። እንደዚሁ በልብሱም በጫማውም በሽቶውም በድሪያውም

እየተገረምሁ አዛዥን የአባቴን ጐረቤት በማቆምና በጥያቄ በማሰልቸት ስንጓዝ ወደምንሔድበት ቤት ደረስን።

እኔን በአደራ የሚቀበሉት የአቶ ውብነህ ወዳጅ ከንግድ ሱቃቸው ተጠርተው መጡና ከአቶ ውብነህ ጋር ተገናኝተው ጥቂት ከተወያዩ በኋላ፤ «ይኸውልህ ይኸ የአቶ ብዙነህ ልጅ ነው» ሲሉ የቤቱ ባለቤት «ኧረግ!» ነው እንዴ? እሳቸውማ ለኔስ ብርቱ ወዳጄ አይደሉ! ና ሳመኝ የኔ አባት» አሉ። እኔም ደስ አያለኝ ቀረብ አልኋቸውና ጉንጬን አገላብጠው ሳሙኝ። ወዲያው «በሉ ወደ ቤት እንግባ» ብለው የቤቱ ባለቤት እየመሩን ወደ ቤት ገባን። በቤቱ ያየሁት ነገር ሁሉም በውጭ እንዳየኋቸው ነገሮች ከማውቀው ነገር የተለየ ሁኖ አገኘሁት።

የመስተንግዶ መጠጥ ቀርቦልን ጥቂት እንደ ጠጣን «እና አሁን ይኸን ልጅ ያመጣሁት ለጊዜው ከዚሁ መጠጊያ ሁነኸው ትምህርት እንዲጀምር ነው» አሉዋቸው አቶ ውብነህ በትካዜና በቅርታ።

የቤቱ ባለቤትም «እንዴ ምናለበት ብዙ ባዶ ክፍል ሞልቷል። የኔም ሁለቱ ልጆቼ ይማራሉ። ከነሱ ጋር እየወጣ እየገባ ይማራል።» አሉ።

አቶ ውብነህ በኅዘን ፊታቸውን ኮፍተር አድርገው «ለቀለቡስ ከነዚያ ከፉ ዘመዶቹ እንደምን እያልሁ አስልክለታለሁ» አሉ።

«አባቱስ?» ሲሉ የቤቱ ባለቤት በድንጋጤ ጠየቁ።

«አባቱና እናቱማ አሁን በቅርብ ሞቱበት» አሉ።

«የመድኃኔ ዓለም ያለህ! ምን አገኛቸው?» አሉ የቤቱ ባለቤት ራሳቸውን በሁለት እጃቸው ይዘው።

«በየግቢውና በየጥቢው የሚነሣው ወረርሽኝ መቸ ሰው የሚያተርፍ መሰለህ። አሁንማ በቀበሌው ሽበት ያወጣ ሰው መቼ የሚገኝ ሆነ።» ሲሉ አቶ ውብነህ አስረዱ።

የቤቱ ባለቤትም «አዬ ወዳጄን! አዬ ጉድ! እንዴት እስከዛሬ አልሰማንም? ምንስ ባንዛመድ አብረን በልተናል ጠጥተናል። ከፉውን ደጉን ተጨዋውተናል አዬ!! «የባዕድ መርዶ የለው» የሚባለው ከንቱ ተረት ለካ እውነት ነውና» አሉ።

አቶ ውብነህም መለስ አድርገው «መቼ ተሰማ ከሞቱ ገና ወር እንኳ አልሞላቸውም። ዘመዶቻቸው አርባቸውን ለማስቆረብ ለድግሱ በመዘጋጀት ላይ ናቸው» አሉዋቸው።

«አዬ ወዲያ ከሞቱ በኋላ ልጆቻቸውን ማሳደግ መጠበቅና ማስተማር እንጂ ለቁና ለተዝካር እንዲሁም ለሙት ዓመት ሲሉ ጥሪታቸውን ጨርሶ ልጆችን በችግር ላይ መጣል ምን ዋጋ አለው?» ሲሉ የቤቱ ባለቤት ተናገሩ።

«አዬ! መጥፎ ዘመዶች ናቸው። ምንም የረቡ ዘመዶች የሏቸውም ለልጆችም የሚያስቡ ሰዎች አይደሉም። ሴትዮዋ በጣም ወላድ ስለ ነበረች ብዙ ሕፃናት አፍስሰው ነው የሞቱት። ከሁሉም የባሰው ድግሞ ራሱን ብቅ አድርጓል የሚባለው ይኸ ብቻ ሲሆን፤ የቀሩት ከርሱ በታች የተወለዱ ነፍስ ያላዋሉ ሕፃናት ናቸው። ደኅና ዘመድ ቢኖር እንኳ የወላጆች ሀብት እንኳንስ ለነሱ ለሌላም ይተርፍ ነበር። ግን መጥፎ ሰዎች ናቸው» ሲሉ አቶ ውብነህ እውነተኛውን የዘመዶቼን ክፋት ተናገሩ።

ይህንንና የቀረውን ብዙ ነገር ከተወያዩ በኋላ ሰውዬው በአደራ ተቀብለውኝ አቶ ውብነህም ወደ ውጭ አውጥተው መክረውና አጽናንተውኝ ወደ ቤታችው ተመለሱ።

# ምዕራፍ ፫።

በዚያ ወራት የውጭ አገር ትምህርት በሀገራችን መስፋፋት መጀመሩ ነበር። ተማሪ እየተለመነና እየተቆላመጠ የሚማርበት ጊዜ ነበር።

ትምህርት ቤት ለመግባት ስጠይቅ የትምህርት ቤቱ ሥራ መሪና ዲሬክተሩ በደስታ ተቀበሉኝ። ደብተርና እርሳስ ወዲያው ተሰጠኝ። በተለይም ደግሞ ዳዊት የደገምሁ፤ ንባብና ጽሕፈት የምችል ሁኜ በመገኘቴ ሥራ መሪው «አንተስ የዛሬ ሦስት ዓመት ወደ አዲስ አበባ ትሔዳለህ አይዞህ በርታ» ብሎ ራሱ ወደምገባበት ክፍል ወሰደኝ። በአንደኛ ክፍል የሚገኙት ልጆች አብዛኛዎቹ ፊደል ቆጣሪዎች ስለ ነበሩ «አንተ እዚህ መሆን የለብህም በዕረፍት ጊዜህ በከፍተኛ ክፍል ካሉት ልጆች እየጠየቅህ ፬ መደቦችንና «A.B.C.Dን» አጥና።» ብሎ ወደ ሁለተኛ ክፍል ወሰደኝ። ከዚያም ለክፍሉ ኃላፊ አስተማሪ «ይህ ልጅ የተማረ ነውና በተለይ የትምህርት ተቀባይነቱን መጠን ተከታተለው በጣም ተቀባይ ከሆነ ፈተና እየሰጠን ከክፍል ወደ ክፍል እናዛውረዋለን።» ካለው በኋላ ወደ ቢሮው ተመለሰ።

ከዚች ቀን ጀምሬ ትምህርቴን በሚገባ ተከታተልሁ። በእውነቱም ትምህርቱ ቀናኝ። ለመጀመሪያ ጊዜ የሞቱት ወላጆቼ ትዝታና በአክስቶቻችንና ባጐቶቻችን ቤቶች ተከፋፍለው የሚገኙት ወንድሞቼና እኅቶቼ ናፍቆት ቀኑን በሐሳብ ሌሊቱን በቅዠት እየመጡብኝ አብዛኛውን ጊዜ በትካዜ እንዳሳልፈው ያስገድዱኝ ነበር።

ነገር ግን ከአደር አደር ሁሉንም ችላ እያልሁ ትምህርቴን በትጋት እከታተል ጀመር። የሞቱትን ወላጆቼን ወይም በሰቀቀን ላይ የሚገኙ እኅቶቼንና ወንድሞቼን ሳላስባቸው እስከ አንድ ወር ድረስ የምቆይበት ጊዜ እንኳን ይመጣ ጀመር። የተጠጋሁባቸው ሰውዬም ምንም እንኳ እንደ አቶ ውብነህ ያሉ ፍጹም ደግ ባይሆኑ በመጠኑ ደኅና ሰው ነበሩ። ከፉዎች ቤተ ዘመዶቼም ምንም እንኳ ይሉኝታ ቢሶች ቢሆኑ ከሞላው የወላጆቼ ሀብት ጥቂት ጥቂት ምጽዋት ይልኩልኝ ነበር።

እንደዚህ ባለ ሁኔታ ፬ ዓመት እንደተማርሁ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለመተላለፍ የሚሰጠውን ፈተና አለፍሁ።

ይህ ሊሆንልኝ የቻለው ፩ኛ/ ትንሽ አማርኛ ነክ ትምህርት ስለ ነበረችኝ ሲሆን ሁለተኛ በዚያ ዘመን የሚሰጠው ትምህርት ከዛሬው የሚቀል ስለ ነበረ ነው።

ፈተናውን ካለፍሁ በኋላ ወደ አዲስ አበባ በመንግሥት ኪሣራ በአኤሮፕላን መጥቼ ወደ አንድ ታላቅ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ገባሁ።

ትምህርት ቤቱ የአዳሪ እንደመሆን መጠን ቀለቤን፤ ልብሴን፤ መኝታዬን፤ በጠቅላላው የሚያስፈልገኝን ነገር ሁሉ የሚችልልኝ መንግሥት ነበር። ከዚህም በቀር እኒያ አይረቡ ዘመዶቼ አዲስ አበባ በከፍተኛ ትምህርት ላይ ነው ያለ ሲባል ስለሰሙ እየፈሩኝና እየጠረጠሩኝ ሔዱ። አንዳንድ ጊዜ መፍራትም መልካም ነው መሰል። በፍርሃት ካልሆነ በበጐ ፈቃድ መሥራት የማያውቁት ዘመዶቼ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሁሉን ነገር መንግሥት ችሎልኝ በምኖርበት ጊዜ በፍርሃት የሚልኩልኝ ገንዘብ ድሮ በቅርባቸው በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በራሴ እየተዳደርሁ በምማርበት ጊዜ ይመጸውቱኝ ከነበረው መቁንን እጅግ ከፍ ያለ ነበር።

ይሁን እንጂ ይህ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በነበርኩበት ጊዜ፤ ከሚያስፈልገኝ ወጭ በላይ ይልኩልኝ የነበረው ሀብት ብዙ መጥፎ ዓመል አለመደኝ እንጂ እጅግም አልጠቀመኝ።

ለምሳሌ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሳለን ብዙዎች ጓደኝኖቻችን መንግሥት በወሰነላቸው መተዳደሪያ በሚገባ ሁነውና አምሮባቸው መንፈሳቸውንና ጤንነታቸውንም ጠብቀው ግን ሲጋራን፤ አልኮልን፤ የቀሩትንም መጥፎ ልምዶች የተማርን በዚህ ጊዜ ነው።

ከዚህም በቀር ማታ ማታ በየሴቶች መደብር መዞርን ስላዘወተርንና ከጥናትም ብዙ ጊዜ ስለምንሰናከል አንዳንድ ጊዜም ከትምህርት ቤትም ከውጭም ስለምንራበሽ በትምህርት ከጓደኞቻችን በታች መሆን ግዴታ ሁኖብን ነበር።

እንደምንም ብዬ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ወደ ፊት ለመቀጠል የምሰናከልበት ሁኔታ ባይኖር ምንም እንኳ ትምህርቴን ወደ ፊት ለመቀጠል የምሰናከልበት ሁኔታ ባይኖር ምንም ላልሠራላቸው እነዚያን ዕድለ ቢሶች እኅቶቼንና ወንድሞቼን ከተበተኑበት እሰበስባለሁ ብዬ በማመካኘት በአንድ መሥሪያ ቤት ወዲያው ሥራ ያዝሁ። ሥራ ገብቼ በሥራዬ እንደተስማማሁ አንድ ጊዜ ፈቃድ ተቀብዬ ወደ ዘመዶቼ ሔድሁና በግድም በውድም የወላጆቼን ሀብትና ርስት ሁሉ በጄ አድርጌ ወኪሎቼንም ሰጥቼ በመጣሁበት ጊዜ ብዙ ችግር አላጋጠመኝም። ለባላገሮች መጉላላት ደንታ የሌላቸው የምክትል ወረዳና የወረዳ ግዛት ሹማምንቶች እንኳ እኔን ለማጉላላት አልደፈሩም።

ነገር ግን እኅቶቼንና፤ ወንድሞቼን፤ ሳያቸው በእውነቱ የኀቶቼና የአክስቶቼ ገረዶችና አሽከሮች መስለውኝ ነበር እንጂ እናቴና አባቴ እንደዚያ ይሳሉላቸው የነበሩት ሕጻናት ናቸው ብዬ አልጠረጠርሁም። ልጆች ወንድማችሁ መጥቷል ተብሎ በተነገራቸው ጊዜ ምንም እንኳ የተለያየነው ገና ትንሽ ሳሉ ቢሆን፤ ጥቂት ጥቂት ያውቁኝ ስለ ነበርና ከዚህም በቀር እንደዚያ በሚበደሉበት ጊዜ ሁሉ ዘመድ ጎረቤት «አይዟችሁ ወንድማችሁ ይደርስላችኋል!» እያለ ያስጠናቸው ስለ ነበር የኔን መምጣት በሰሙ ጊዜ ከያሉበት እየተሯሯጡ መጡና በሥራ አከላቴ እየተጠማጠሙ ይስሙኝ ጀመር። ከሁሉም የሚፀፅተኝና ልቤን እንደ እሳት የሚያቃጥለኝ፤ ያች ትንሿ እኅቴ የክረምት ማገዶ የሚሆን ጥፍጥፍ ለመሥራት በእጅዋም በእግሯም የከብት እበት ስታላቁጥ በሕጻንነቷ የነበረችበትን መከራ ላስታውሰው ነው።

ልጆች ክብብ አድርገውኝ ተቀምጠው በናፍቆት ዓይን ዓይኔን ሲመለከቱኝና «ከመከራ አድነን» የሚል ልመና በግንባራቸው ተስሎ ሲቅበዘበዙ የተመለከተ ሰው ልቡ ድንጋይ ካልሆነ በስተቀር ዕንባውን የሚገታበት ኃይል ሊያገኝ አይችልም ነበር።

ነገር ግን ምንም ያለ መጠን መበደላቸውና መጎሳቆላቸው ግልጽ ሁኖ ቢታየኝ፤ ምንም ልቤ ቢያዝን ያደረግሁላቸው አንዳች ነገር የለም። ብቻ የማልፈጽመውን ተስፋ ሰጥቼ በከንቱ አጓጓቻቸው ተመለስሁ። ትንሿ እኅቴም «ወንድም ዓለም ጨክነህ ትተኸኝ መሔድህ ነወይ?» እያለች ስታለቅስ አይዛችሁ አሁን መጥቼ ሁሉን በሚገባ አደራጅቼ አስቀምጣችኋለሁ አልሁና ወደ ሥራዬ ተመለስሁ። ያልታደሉት የሙት ልጆችም የናት የአባታቸው ሀብት ሞልቶ የሚሰበባቸውና የሚያስብላቸው ባለ መኖሩ የአክስትና የአጎት ገረድና አሽከር ከገረድም ገረድ፤ ከአሽከርም አሽከር፤ ደመወዝ በመጠየቅ ፈንታ ጉልበታቸውንና የወላጆቻቸውን ሀብት የሚገብሩ ገረዶችና አሽከሮች ሁነው ቀሩ።

እኔም ያደረብኝ ርኩስ መንፈስ ዛሬ ጐልቶ ሊታየኝ ያንጊዜ አልታየኝም ነበርና የናቴን ልጆች ሥቃይ ላስታውሰው አልቻልሁም ነበር። ከጋራ ርስታችን ተሰብስቦ ለኔ ብቻ

የሚጫነውን እህልና የቀረውንም ሀብት እየተረከብሁ «ላለው ይጨመርለታል» እንደሚባለውም ሁሉ በሥራዬና በደመወዜ እያደግሁ በመሔዴ ጌትነትን እንጂ ደሀ ቤተ ዘመድን ለማሰብ ጊዜ አላገኘሁም።

ከዚያ በኋላም «ዓይን ከማየቱ የተነሣ ልብ ያመነዝራል» እንደሚባለው፤ የብዙ ጌቶችን ፎቆችና እኔ ሽሚዜን ልለውጥ በማልችልበት አጭር ጊዜ ውስጥ ሊለዋወጡዋቸው የሚችሉትን ብዙ መኪናዎች በማየት ከነሱ ለመድረስ መጣደፍን እንጂ የወደቀ የሙት ልጅን ማን ቢያስብ?።

ይህን በመሰለው መጥፎ የውድድር በሽታ የናቴን ልጆች እንደወደቁ ትቼ የጋራ ሀብታቸውንም ቀምቼ ጥቅሜንና ካፒታሊስትነቴን ከፍ ለማድረግ ከይሉኝታ ውጭ ሁኜ እባክን ጀመር። የከተማ ካስፋፋሁ በኋላ፤ ከሁለት ከሶስት ቦታዎች ላይ የድንጋይ ቤት ጀመርሁ፤ የናቴ ልጆች ግን ድንጋዮች ሁነው መቅረታቸውና አንድ ቀን ደስ ሳይላቸው በመንገላታት እንደቆዩ መሞታቸው ጉዳቴና በሰላም የማያስሞት ጸጸቴ መሆኑ በዚያ ጊዜ አልታሰበኝም።

በዚህ መሠረት ከሁሉ እደርስ እደርስ ስል ሁሉንም ነገር ትቼ ይሉኝታ የሌለኝ ቀጥቃጣ ሰው ሆንሁ።

ለቀን ሠራተኞች የሚገባውን ጥቂት ገንዘብ ለመስጠት እንኳ ብዙ ጭቅጭቅ እስኪደርስብኝ ድረስ ማልመጥ ቢቻለኝም አጭበርብሬ የድሆችን የጉልበት፤ ዋጋ ማስቀረት የተለመደና የማላፍርበት ተግባሬ ሆኖ ነበር።

ከዚህም በቀር ከማንኛውም ዘመድና ወዳጅ አሥር ሣንቲም ይበልጣል የሚል እምነት አድሮብኝ ለወዳጆቼም ሆነ ለዘመዶቼ የአምስት ሣንቲም ያህል ክብር አልሰጣቸውም ነበር።

አትድከሙ እውነቱን ልንገራችሁ፤ ልቤ የነበረው ከታላላቆች ሀብታሞች ለመድረስ ካለኝ ምኞት ጋር እንጂ ከኔ ጋር አልነበረም። ራሴን የማዝዝበትና ሰው መሆኔን የማስታውቅበት አእምሮዬም ጠፍቶ ነበር።

# ምዕራፍ ፮።

በዚህ ሁኔታ ስኖር የትምህርት ደረጃዬን ከፍ አድርጌ፤ በደመወዜም ሆነ በሥራዬ የበለጠ ዕድገት ለማግኘት መጣጣሬን ጀመርሁ።

ምኞቴም ተፈጽሞ በዩናይትድ እስቴትስ ኦፍ አሜሪካ የነፃ ትምህርት (ስኮላርሽፕ) ተገኝቶልኝ ለትምህርት ወደ አሜሪካ ሄድሁ። በዚያም ፬ ዓመት ተምሬ በኢኮኖሚ ትምህርት ቢ ኤ (B.A) የሚሉትን የትምህርት ደረጃ መግለጫ ወረቀት ተቀብዬ ወዳገሬ ተመለስሁ። አገሬ አሏት ከሚባሉት የተማሩ ወጣቶች መካከልም ተቆጠርሁ። ግን ልቆጠር አይገባኝም ነበር። እኔ ከተማሩትም ሆነ ካልተማሩት መልካም ሰዎች ጋር መቆጠር አይገባኝም። የኔ ጓደኞች ተብለው ሊቆጠሩ የሚገባቸው ተግባራቸውን የዘነጉ፤ በሥራ ሳይሆን በስምና በወግ ብቻ ለመኖር የሚፈልጉ አቃጣፊዎች ብቻ ናቸው። የኔ ጓደኞች «ካልጋ ሲሉት ካመድ» ለድግ ሲመኙት ለክፋት የሚውሉት ናቸው። አገሬ ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ መንግሥት እኔን ለማስተማር በመድከማቸው አልተሳሳቱም በትምህርት ተወልደው መልካም የሚሠሩና፤ ለወገናቸው የሚያስቡ ሰዎች መኖራቸውን ስላዩ፤ እንደኔ ያለ አንዳንድ አጭበርባሪና «ከጅ አይሻል ዶማ» መኖሩን ለመረዳት ጊዜ አላገኙም። ወይም አማላጆችና መራጮች አጭበርብረዋቸዋል። የሌሎችን ክፋትና ደግነት ልተውና የራሴን ልናዘዝ። ያለችኝን አጭር ጊዜም በከንቱ አላባክናት፤ ብዙውን ጊዜዬን በከንቱ ማባከኔ ይበቃኛል። በአሜሪካ አገር በቆየሁበት ጊዜ ላጠናውና ይዤው ልመጣ የሚገባኝ ብዙ ነገር ነበር። በየጊዜው በዘር ልዩነት ምክንያት የደረሱብኝን መጉላላቶች በማስታወስ ዘሬንና ወገኔን የማክብር ስሜት በበለጠ ሊያድርብኝ ይገባኝ ነበር። በዚያ አገር ያለውን ሁሉ ዕድገት ለማግኘት የስንት ሰዎች ጥረት ማስፈለጉን በመገንዘብ፤ ለሀገሬና ለወገኖቼ የመሻሻል ዕድገት በቆራጥነት መሥራት ያለብኝ መሆኑን ማወቅ ነበረብኝ። ተምሬዋለሁ በምለው ነገር አለመሥራት በተማሩትም ሆነ ባልተማሩት ሰዎች ፊት ማሳፈሩን ልገንዘበው ይገባኝ ነበር። ግን አልተገነዘብሁትም። ለትምህርት የተወሰልኝ ጊዜ እንዳለቀ፤ ካሜሪካ ወስጄ ከሁሉ አስቀድሜ ባገሬ ልሠራበት የተመኘሁትን፤ ከቂጥ በጣም ዝቅ ከቋንጃ ከፍ ያለውን ቀጭንና ረጂም ኮት ለብሼ እግሬን ጠረጴዛ ላይ ዘርግቼ ረጂምና ወፍራም ሲጋራ ጉርሼ who cares!......... go to hell ማለትን ነበር። አገሬ እኔን በመሰሉ ሰዎች ከሥራለች። ግን ከኔ የተሻሉ ደኅኖች ከተማሩትም ብዙ ካልተምሩትም መካከል ስላሉዋት በኔ ሁኔታ ተስፋ መቁረጥና በትምህርት ያላትን እምነት መለወጥ የለባትም።

ማሳውን አለስልሶ ስንዴ የዘራ ገበሬ በለሰለሰው ማሳው ላይ ስንዴ ብቻ ሳይሆን አረምና እንክርዳድ አብሮ መብቀሉን ማወቅ አለበት። በአንድ ነገር ውስጥ ንጹሕ ፍሬ ብቻ ይገኛል ብሎ መጠበቅ ስኅተት ነው። ሁልጊዜ ከጠቃሚ ነገሮች ጋር መጥፎ ነገሮች መኖራቸው የተረጋገጠ ነው። ትምህርትም ብዙ አዋቂዎችን፤ ፈላስፎችንና አዲስ ነገር አግኝዎችን የሚያበረክት ሜዳ ሲሆን አንዳንዴ እንደኔ ያሉ ሸክሞችን መፍጠሩን መካድ የተፈጥሮን ጣጣዎች እንደመካድ ይቆጥራል።

ለምሳሌ የሰውን ችግር፤ በሽታን፤ ድካምንና ድንቁርናን የሚያጠፉ ጠቃሚ ነገሮች ካዋቂዎች ሲገኙ የሰው ልጆች መጨረሻና የሰው ልጆች ነፃነትና መብት መደምሰሻ የሆኑ የጥፋት ኃይሎችና ዘዴዎች ባዋቂዎች መፈጠራቸውን ማመን ይገባል። ሌብነት፤ መግደልና ሌሎች ወንጀሎች እንኳ በትምህርት እንደተራቀቁ ማወቅ ተገቢ ነው። ልዩነቱ የተገኘ ዕውቀትን ለበጐ ነገር በማዋልና ለክፉ ነገር በማዋል ነው እንጂ «አወቅሁ» በማለት ብቻ ልዩነት የለም። ስለዚህ ጥቂት ከተማርሁ ስኅተት የለብኝም ማለት እንደኔ ደንቆሮ መሆን ነው። አንዱ ተምሮአል የሚባል ሰው ከተሳሳተ ሁሉም መጥፎ ይሆናል ብሎ መገመትና ትምህርትን መቃወምም የባሰ ድንቁርና ነው።

ወደሥረ ነገሬ ልመለስና የኔውን ታሪክ ልቀጥል። እኔ ሁልጊዜም የመጥፎዎች ወገን ነኝ። ተምሬአለሁ ብዬ በመብለጥለጥ ከተማሩት ጋር ለመዋል ስፈልግ በሌላው በኩል ደግሞ አልተማሩም የሚባሉት ሰዎች የሚጠቀሙበትን የኑሮ ዘዴ በጣም እከታተል ነበር። ተምሯል ተብዬ በመገመት ከደኅና የሥራ ቦታ ላይ እንደተቀመጥሁ በገንዘቧና በወገኖቿ የምትደግፈኝ ሚስት ደግሞ ፈለግሁ። ያገባኋት ሚስት የታወቀች የሀብታም ዘር ነበረች እንጂ የማወቅና የመሻሻል ደጋፊ አልነበረችም። በዓለም የምታውቀው ታላቅ ነገር ሹመት ብቻ ሲሆን በሀብትም ምንጭነት በኩል የምታውቃቸው ነገሮች ደግሞ የቤት ኪራይ መሰብሰብና ከርስት ብዙ ሀብት ማግኘት ነበር። እኔም ተማርሁ ልባል እንጂ ከዚህ የተሻለ እምነት ስላልነበረኝ እሷ ያድጋል ይሾማል የሚል ተስፋ ጥላብኝ እኔም ጥሩ የሀብት ምንጭ ትሆነኛለች የሚል ተስፋ አሳድሬባት ተስማምተን ተጋባን።

ሀብት ብዙ መንገዶች ከፍቶ ወደኛ መጣ። እሷም እኔም የሀብት መጠራቀሚያ ባንኮች ሆንነ። እንደነገርኋችሁ የናት አባቴን ብዙ እርስት እኅቶቼንና ወንድሞቼን ነጥቄ ለብቻዬ የወረስሁ ከመሆኔ በላይ በግዢ፤ በወለድ አግድ፤ እንዲሁም አንዳንድ መካን አረጋውያኖችን እጦራችኋለሁ እያልሁ ርስታቸውን በፊርማ በመውረስ የሰበሰብሁት መሬት መጠን አልነበረውም ምናልባት እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እኔ የያዝሁትን ያህል መሬት ለመያዝ ቢፈልግ ያገራችን መሬት ለጥቂት ሺ ሰዎች ብቻ ሁኖ ለቀረው ሕዝብ ሌላ አገር መፈለግ ግድ በሆነ ነበር። ግን ደግነቱ አንዳንዳችን ይህን ያህል እንደመሳመጣችን መጠን ብዙዎች ለሁሉም ግድ አልነበራቸውም። ለምሳሌ ከኔ ዘመዶች መካከል ለከፍተኛ ክብር ለብዙ ሀብትና ለሰፊ ርስት የምቃተለው እኔ ብቻ ስሆን የቀሩት ዘመዶቼ በንፍሮም ሆነ በቆሎ ሆዳቸው ሞልቶ ካደረ ሌላ ዓለም አለ ብለው አያስቡም። ይህም ለኔና እኔን ለመሳሰሉት ጮሌዎች ገፈፉ ምቹ ጐዳና ሆኖልን ነበር።

በዚያም ብዬ በዚህ በኔም ብዬ በባለቤቴ የያዝሁት መሬት በየቀበሌውና በየጠቅላይ ግዛቱ የተከፋፈለ ሳይሆን ባንድ ላይ ቢሆን ኑሮ ጭነት የበዛበት ትሬንታ ኳትሮ ካሚዎን ባንድ ቀን ሊያቋርጠው የማይችል ሰፊ አገር በሆነ ነበር። ነገር ግን ደግነቱ በየቦታው

የተከፋፈለ በመሆኑ ከማሳጣት አድኖኛል። ከዚህ ላይ አንድ ራሴን በራሴ የሚያስጠላኝና የሚያስንቀኝ ነገር አለ። እኔ እንደዚህ ለግል ጥቅሜ እየተሳመጥሁ «የመሬት ይዞታ ለምን አይሻሻልም? በሀገራችን ውስጥ የግል ጥቅማቸውን በመጠኑ መሥዋዕት እያደረጉ ለሀገራቸው ጥቅም የሚሠሩ ሰዎች በብዛት ለምን አይገኙም?» የሚልና ሌላም ይህን የመሰለ ወሬ በተነሣ ጊዜ አስቀድሜ አፌን የማሾልና ሌሎችን የምነቅፍ እኔ ነበርሁ። «ማን ይሠራል?» እያልሁ ኃላፊነቱን ሁሉ በሌሎች ላይ ለመከመርና አጭበርባሪውን ራሴን ነፃ ለማድረግ የምጣጣር አስመሳይ፤ እራሴን ወዳጅ በማንኛውም መንገድ ጥቅሜ እንዳያመልጠኝ የምባክን ቀጣፊ በርግጥ እኔ ነበርኩ። (በሞት አፋፍ ላይ መሆኔ ጊዜ አልሰጠኝም እንጂ በእውነት ከተነጋገርን ያንድ አገርን ልማትስ ሆነ ጉዳት ባንድ ሰው ወይም በጥቂት ሰዎች ኃላፊነት ላይ ልንጥል ይገባል?» ነገር ግን የተሰጠኝን ሥራም አልሠራው ነበር። ለሥራ መሯሯጥ የዕለት ትዳራቸውን ለማሸነፍ ለሚባክኑ ድሆች እንጂ እንደኔ በውቀቱና በሀብቱ እንዲሁም በባለ ጋሻ ሚስቱ ለሚመካ ሰው አስፈላጊ መስሎ ስላልታየኝ በ፫ ሰዓት ግድም ወደ ቢሮዬ ሂጄ ተላላኪዎቼን ጥቂት ከገላመጥሁ በኋላ ገብቼ እቀመጥና ቆራጭ ፈላጬ የሆነውንና የሥልጣኗ ተገዢ የሆንሁላትን ሚስቴን አግብቼ የግል ነፃነቴን ከማጣቴ በፊት በየፓርቲው ከተዋወቅኋቸው ጓደኞቼ አስር ያህል የቴሌፎን ጥሪዎች ተቀብዬ እኔም በበኩሌ ፲፫ ጊዜ ያህል ጠርቼ ኧኸ? እንደምን አለሽ?....... እንደምንድ ነህ? ካልሁ በኋላ ሁለት ደብዳቤዎችን ፈርሜ ሶስት ያህል ጥቂት ሰርዤና እንደገና እንዲጻፍ አዝዤ እንዲሁም የቀረውን በሌላ ቀን እንዲቀርብ አድርጌ የተመለስሁለት በበነጋው ከቀኑ እስከ አምስት ሰዓት ተኩል መተኛት አለብኝ። ቁርሴንም ካልጋዬ እንደተንጠልጠልሁ ብበላ እወዳለሁ። ምን ሁነህ ነበር? ብሎ የሚጠይቅ ከተገኘም መቼም ይሉኝታ ቀርቷልና «ትናንት ሥራ በዝቶብኝ» እላለሁ። አዬ ሁሉን ቻይ ፈጣሪ! እዬ እውነተኛው አምላክ! ራሴን እውነተኛ ሌሎችን ሐሰተኞች፤ እኔን አዋቂ ሌሎችን ደንቆሮ እያደረግሁ ስናገርና በሥራ ግን እኔ ከሌሎች የባስሁ መጥፎ ሁኜ ስገኝ እኔን እስከ ዛሬ ታግሠህ መኖርህ እንዴት ቸር ብትሆን ነው? የሆነው ሆኖ በሰውም ሆነ በእግዚአብሔር ፊት ለፈጸምኋቸው ወንጀሎች ተገቢ ቅጣቴን አግኝቻለሁና ሳትበሳጩ አዳምጡኝ።

ለማንኛውም ዓይነት ክፋትና ጭካኔ የተዘጋጀሁ ስሆን ላደርገው የማልፈልገውን አንድ ነገር ብቻ ነበር። ይኸውም የገዛ ወገናቸውን በዘር በነገድ በሃይማኖት በቋንቋና በጠቅላይ ግዛት ሳይቀር ከሚከፋፈሉት ሰዎች ጋር በዚህ ተግባር ተከፋይ መሆን ነው። ይሁን እንጂ ይህንን የማላደርገውም ከራሴ በቀር ማንንም፤ የናቴን ልጆች እንኳ የማልወድ በመሆኔ እንጂ የወገኖቼን ሕብረት በመፈለግ ያደረግሁት ነገር በለመሆኑ ልመሰገንበት የሚገባ አይደለም። ብሎም ከጊዜ በኋላ በዚህ ተግባርም ገብቼበት ነበር። ምንም እንኳ ምስኪኖች እኅቶቼንና ወንድሞቼን ለመርዳት ባያስወድደኝ እመቤቴ የሆነችውን፤ የሚስቴን ዘመዶች መርዳት ግዴታዬ ሁኖ ስላገኘሁት የዕለት ተግባሬን አጋማሽ እነሱን ለማገልገል

ወስኘው ነበር። እቢሮዬ ሁኜ ችሎታ ይኑረውም አይኑረው አንዱን የሚስቴን ዘመድ በአንድ ደኅና ደመወዝ ባለው ሥራ ላይ ለማዋል በስልክ ሰዎችን ሳደርቅ ከመዋሌ በቀር ከመንግሥት የሚሰጠኝን ቤንዚን የምጨርሰው የሚስቴን ዘመዶች ደኅና ሥራ ለማስያዝ ወደ የመሥሪያ ቤቱ በመሯሯጥ ነበር።

ያውም ከውለታ ላትቆጥርልኝና ያን አጥቂ ምላሷን ላትቀንስልኝ ነው። በዚህ ምክንያት ከደረሱብኝ አሳፋሪ ነገሮች አንዱን ልነግራችሁ እወዳለሁ። አንድ ጊዜ ወዳጄ የሆነ የፔርሶኔል ሹም ባለበት መስሪያ ቤት ክፍት ሥራ ስለ ነበረ ለሥራው ተስማሚ የሆነና ብቂ ችሎታ ያለው አንድ ወጣት ፈተናውን አልፎ በተያዥ ፍለጋ ምክንያት ፪ ቀኖች ስላሳለፈ ይህን ምክንያት በማድረግ የሚስቴን የአጐት ልጅ እንዲገባ አስደረግሁ።

ወጣቱም ጉዳዩን ስለደረሰበት ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የመረረ ደብዳቤ በፖስታ ቤት ላከልኝ።

«ያልዘሩት በቀል ወንድሜ ሆይ!»

«ሥራህን ዕውቀትህንና ሥልጣንህን አየንልህ! ኢትዮጵያ ባንተ የመሻሻል ተስፋ አድርጋብህ ነበር። አንተ ግን ተስፋ ሊጣልብህ የሚቻል ሰው አይደለህም። ያለፈውን የባላባትነትና የዘር ታላቅነት ትቃወማለህ። ሰው በዘርና በወግ እየተመካ ታላቅነትን ማግኘት አይገባውም ትላለህ! መልካም ብለሃል! ነገር ግን ከዚህ ጋር አንድ ነገር ጨምረህ ማወቅ ይገባሃል። ሥራውና ውጤቱ ባልታየ ትምህርት መመካትም በዘርና በወግ ከመመካት አይሻልም። ትምህርት፤ የዕውቀት፤ የርኅራሄ፤ የጨዋነትና የግብረ ገብነት መሸመቻ ገበያ ነው እንጂ የመብለጥለጫ የራስ ብቻ መመኪያ የማጥቂያ መሣሪያ አይደለም። ካንተ የበለጠና ካንተም ያነሰ የትምህርት ደረጃ ካላቸው ኢትዮጵያውያን ወንድሞችህ ልትማረው የንጉሠ ነገሥት ከኢትዮጵያ ሕዝብ በተገኘው ግብር አንተን ማስተማሩ የሀገሪቱ አገልጋይ እንድትሆን እንጂ የወግ ሙያህን ባስተማረህ ሕዝብ ላይ እንድትነፋና ትከሻህን አሳብጠህ የዘርና የወገን ልዩነት እንድትፈጥር አይደለም። ትምህርት የምትፈልግ ብትሆን የአንድ ሊቅ ቃል ልንገርህ። በመላው ዓለም የታወቀውና ስመገናና የሆነው ሳይንቲስ ፕሮፌሰር አልበርት አይንስታይን፤ የእስራኤል ፕሬዘዴንት እንዲሆን በተጠየቀ ጊዜ ሁሉ «ስለሳይንቲፊክ ጣጣዎች ብትጠይቁኝ ለኔ ተስማሚ ናቸው ሰዎችን ለመራት ግን የተፈጥሮ ስጦታ ወይም አስፈላጊ የሆነው ልምድ የለኝም።» ሲል ችሎታውን እየወሰነ በመናገር ጥያቄዎችን ሳይቀበል ቀርቷል። እንዲሁም ሶክራትስን ያህል ታላቅ ፈላስፋ «አንድ ሰው የማያውቀውን ነገር አውቀዋለሁ ብሎ ማሰቡ በእርግጥ የተጨበጠ ድንቁርና ነው። ...... የኔ ዕውቀት አላዋቂ መሆኔን ማወቄ ብቻ ነው» ብሏል። አንተ ግን በትንሿ ዕውቀትህ እየተመካህ በምታደርገው ስኅተት የደንቆሮ ደንቆሮ ሁነሃል። ትምህርት

ተምረው መልካም ለመሥራት ለሚጣጣሩት ወገኖችህ ማረፊያ አትሁን። በአእምሮህና በአካልህ የምትሠራው ሥራ ችሎታህን ካልመሰከረልህ የያዝኸው ወረቀት የእውቀትህ መሆኑ ቀርቶ የድንቁርናህ ምስክር ይሆንብሃል። የተማርኸው ትምህርት ከዚህ ከዚህ ግብዝነት እንኳ ላያድንህ ነውን? ተምሬአለሁ የምትል ስትሆን በችሎታ በማመን ፈንታ በዝምድና እንዴት ታምናለህ? የተማሩ ወገኖቼ ሁሉ ካንተ መንፈስ እንደሚርቁ ተስፋ አላለኝ ባንተና እንዳንተ ባሉ አንዳንድ ያልዘሩ በቀሎች ተስፋ አልቆርጥም። የኢትዮጵያ አምላክ ልብ ይስጥህ ደህና ሁን። እኔም ዘመድ ሳይሆን ሠራተኛ የሚፈልግ ሥራ አግኝቼ ገባሁል! አንተም ከሚስትህ ጋር የአንድ ቀን ሰላም እንኳ ብታገኝ እንኳን መማለጃ አገኘህ!» ይህንና በዚህ ልገልጸው ያልቻልሁትን ብዙ ነገር ጽፎ ሲልክልኝ በጣም ተናደድሁ። ቢሆንም ምንም ላደርገው አልቻልሁ። በማኛውም መንገድ ብዬ እኔ ታላቅና ሀብታም ሰው ከመሆኔ አልወረድሁም ሁሉም ሞልቶኝ ነበር። ችግሩ ከሚስት ላይ ነበር። ለዘመዶችዋና ለገንዘቧ ብዬ ያገባኋት ሚስት መፈጠሬን ታስጠላኝ ነበር። አንድ ቃል ተናግሬ በአሥር ቃላት ያሸበረቀ ዘመናዊ ስድብን መሸመት የዕለት ጉርሻዬ ሲሆን፤ ጥፊው የሚርቅልኝም ስንቀው የነበረው የናቶቻችን ባልን የማክበር ባህል እየያዘልኝ ነው። ሚስቴ ከዚያ ሁሉ ጥጋቧ በላይ እንደኔ ወደ አሜሪካ ሂዳ ብትመለስ ኑሮ በጥፊ ከመላገንም እንደማትመለስ ጥርጥር የለበትም። በጠቅላላው የኔ ባልነት የሷ ሚስትነት የሚታወቀው እሷ የሴት ልብስ እኔ የወንድ ልብስ እየለበስን በመሄዳችን ብቻ እንጂ ሌላው ሁኔታችን ሁሉ እኔ ሴት እሷ ወንድ ሁነን መኖራችንን እኔ ብቻ ሳልሆን ጐረቤት ሁሉ ያውቀዋል። ከሁሉም ትዝ የሚለኝ አንድ ቀን ቅብጥ ብዬ «ከዘመዶችሽ ሠፈር ራቅ ብሎ በሚገኘው ቤታችን እንኑር» የሚል ጥያቄ አቅርቤላት ያወረደችብኝ የስድብ መዓት ነው። ፊቷን ከኔ መለስ አድርጋ ያን ኮሶ ግንባሯን ከቋጠረች በኋላ በጥቁር ሽርጥ የታበተ ደንደሳም ቂጧን እያገላበጠች «ዘሎ ገባ! በቅቶት እንደሆን እይሄድም?!» ካለች በኋላ ፊቷን ወደኔ መለስ አደረገችና «ምን ታወራለህ ከፈለገህ አትደርስም? ማን ከለከለህ? እኔ እለምንሃለሁ እኔ?! ማናለ ዛሬማ ተደላድለሃል የፈለግኸውን ሁሉ አግኝተሃል» አለችኝ። እኔም መለስሁና «እንዴ ምን ታወሪያለሽ በሥራዬ ባድግ በዕውቀቴ ነው። ሀብቱም ከወላጆቼ የወረስሁትና በጥረቴ ያገኘሁት ነው። ካንቺ የተረፈኝ ምኑ ነው?» አልኋት።

ለውበት ሳይሆን ለግልምጫ አውቆ የተፈጠረ የሚመስለውን ትልልቅ ዓይኗን እያጉረጠረጠች «ኧረ ይኸ ይሉኝ አይል! በውቀታቸውና በጠባያቸው ካንተ የሚበልጡ ትምህርትን ከዕውቀት ጠባይን ከቅንነት አስተባብሮ የሰጣቸው ብዙ ሰዎች በሀብትስ ሆነ በደረጃ ካንተ በታች ሁነው ይገኙ የለም ወይ? አንተ የበላህበትን ወጪት ሰባሪ! በራስህ የምትተማመን ሰው ብትሆን የኔ ጥገኛ መሆንን ምን አስመኘህ? በል ፎክር እኔን መሰላል አድርገህ ከፈለግኸው ደረጃ ላይ ወጥተሃል» አለችኝ «ኧረ እኔስ ያገባሁ ወድጄሽ እንጂ ለሀብትሽ ብዬ አልነበረም» አልሁ! «ወድጄሽ?» አለች በጩኸት ጐረቤት እስኪሰማና

እስካፍር ድረስ «ወድጀሽ? ግንድ ያዋድልኝ! ግጥ ትሆኝኝ ብዬ! ላድግብሽ! ልከብርብሽ ብዬ አትልም? ለመሆኑ ለጥቅም ካልሆነ የምትወደው ነገር አለህ? ትምህርቱንም በስሙ ልትጠቀምበት እንጂ ወደህ አልተማርኸውም! ውሻ! «አለችኝ። ሁሉ ነገር ሞልቶልኝ የምበሳጨውና የምናደደው በሚስቴ ጠባይ ብቻ ነበር።

# ምዕራፍ ፯።

እንደዚህ ባለው ሚስቴን የመፍራት ችግርና ብስጭት እየተሠቃየሁ ስኖር እንኳን ከገጠር ያሉ ያልሠለጠኑ ዘመዶቼን ልረዳ፤ እኔም መድረሻ ጠፍቶኝ ነበር። በሁሉም የተሳካልኝ ዕድል፤ በሚስት ብቻ ተበላሽቶብኝ ደስታዬ በኃዘን ተለውጦ በውጭ ታላቅ ሰው በቤት የሚስ ምላስ ያስመረረኝ ሁኜ በነበርሁበት ጊዜ ይግረመው፤ ብለው አንዱ ወንድሜና ሁለቱ ታናናሾች እኅቶቼ እኔን ለመጠየቅ ወደ ከተማ መጡ። የለበሱት ልብስ በጣም ከማደፉ በላይ፤ አልፎ አልፎ የተቀደደና በክር ኃይል የተያዘ ነበር። ይኸው ልብሳቸውም ለቀንም ለሌሊትም ለክትም፤ ለዘወትርም አድርገው የሚለብሱት ከአካላቸው የተቆራኘ ነው። የወንድሜ እግር ወደ ተጠመነው የእርሻ መሬት ቶሎ ለመድረስ ገና በሌሊት ተነሥቶ በውርጭ ያለ ጫማ የሚሔድ በመሆኑ የተረከዙ ንቃቃ የሚያዝያ ወራቱን፤ የዋልካ መሬት ንቃቃት ይመስላል። ጠዋት ተነስቶ በሚጓዝበት ጊዜም የእግሩ ንቃቃቶች ደም እየተፉ ይታያሉ። እንዲሁም እኅቶቼ በጣም ተጐድተውና ተጐሳቁለው ይታዩ ነበር። በተለይም የመጨረሻዋ ትንሽ እኅቴ አይመስሉ መስላ ነበረች። የከንፈሯ ማረ፤ የእግሯና የእጅዋ መሻከር የጠጉሯ መከስከስ የሞት ጥላ በላይዋ ላይ እንዳረፈ ያሳስብ ነበር። እንደዚህ ባለ ሁኔታ የሚታዩ ቤተ ዘመዶቼ ለዕለቱ እኔን ፈልገው ሳያገኙ ድሮ ወደሚያውቁት ወደ አንድ ዘመዳችን የሆነች ሴትዮ ቤት ደርሰው ካረፉ በኋላ በበነጋው ወንድሜ ብቻ እኔን ለመፈለግ ወደ ሥራዬ ቦታ መጣ። መጥቶ እኔን ለመገናኘት በጠየቀ ጊዜም ከውጭ የቆሙት ተላላኪዎች መግባት አይቻልም ቆይ ልንነገርልህ ብለውት ከውጭ አቆዩትና ስወጣ አገኘሁት። እሱም ባየኝ ጊዜ ጉንጬን አገላብጦ ይስመኛል ብሎ በጣም ጓጉቶ እንደ ነበረ ሁኔታው ሳይመሰክርብኝ አላለፈም። ነገር ግን እኔ ንክች አላደረግሁትም። ብቻ እንደምን አላችሁ? አገር ደኅና ነው? የሚል የተራቀቀ ጥያቄ ካቀረብኩለት በኋላ ታዲያ የት አርፈኻል? አልሁት። እሱም አንገቱን ወደ መሬት ቀለስ አድርጎ «ከእማማ ታደገች ቤት ነው የቆየነው። ቀረብሽና አዘነችም። መጥተዋል። አለኝ። «ምን ሊያደርጉ?» ብዬ ብጠይቀው ደግሞ «ስለናፈቅኸን አንተን ልንጠይቅ ነዋ» አለኝ። በእውነቱ ይህን ሲለኝ ልቤ ማዘኑ አልቀረም። ነገር ግን ያቺ በክፉ ቀን ቀብጬ ያገባኋት ሴት እንኳን እንደዚህ ያሉትን፤ ሌሎችንም ቢሆን የኔን ዘመዶች በጠቅላላው ስለማትወድ ሆዴ እያዘነ «ለመሆኑ

ስንቅ አላችሁ?» አልሁት። እሱም መለሰና «አዎ! የስንዴ ዳቦ ና የበቆሎና የገብስ ዳቦ ዳቦ ቆሎ በስልቻ ይዘናል» አለኝ። «መኝታስ?» ብለው ደግሞ «እማማ ታደገች ደግ ሰው ናት፤ ከማድ ቤት አንዱን ክፍል ሰጥታ ገለባ የሚመስል ነገር የሞላበት ጆንያና የሰኔል ምንጣፍ ሰጥታን እንዲህ አይምሰልህ በጣም ተመችቶን ነው የቆየን፤ ደግሞ አምላኬ አንተን ቶሎ አስገኘኝ» አለኝ። ይህን ከተባባልን በኋላ ቤቴን ወስጄ እንደማላሳየውና ወዲያው እኅቶቼን አምጣልኝ ብዬ እንደምልከው በመተማመን ዓይን ዓይኔን እየተመለከተ በኋላዬ ሲከተል፤ ጫማ ሳስጠርግ ከመነዘርኩት ብር ፳፫ ሣንቲም ከኪሴ አውጥቼ እንካ በዚህ ምሳህን ብላ፤ ከነገ ወዲያ በስቲያ እዚህ ድረስ ናና እነማሚቴንም ሔደን እንዳያቸው ብዬው መኪናዬ ገባሁና ዘወር ብዬ ሳላየው መንገዴን ቀጠልኩ። በዚህ ጊዜ ምን ያህል ዕንባ አልቅሶ እንደሆነ እግዚአብሔር ይወቀው። በኋላም ከነገ ወዲያ በስቲያ ብዬው ስለ ነበር፤ በሦስተኛው ቀን ሥራ ከመግባቴ በፊት እቢሮዬ በር ድረስ መጥቶ ቆየኝ። ነገር ግን «እንዴት አደርህ?» በማለት ብቻ አልፌው ወደ ቢሮዬ ገባሁና እስከ ፯ ሰዓት ድረስ እውጭ ሳስጠብቀው ቆየሁ። በሰባት ሰዓት ለምሳ ስወጣ «ወንድም ዓለም እነቀርብሽም መጥተው በግንቡ ሥር ተቀምጠው ይጠብቁሃል እኮ!!» አለኝ። እኔም «ታዲያ አሁን በምሳ ሰዓት ነው የምታመጣቸው?» ስለው ጊዜ ያመጣኋቸውስ ጧት ነው። ግን ቢሆንስ ዘመድ በምሳ ጊዜ መምጣቱ ያስደስታል እንጂ ያስከፋል?» አለኝ ሳቅ እያለ የዋሁ የናቴ ልጅ! ፈረንጅ መሆኔም አልገባው! እኔም ቀስ ብዬ አሳብ የለሽ ካልሁ በኋላ ግንባሬን ቁጥር አድርጌ ልጆች ወደ ተቀመጡበት ሔድሁና ሊስሙኝ በናፍቆት ቀረብ ሲሉ እጃቸውን እየጨበጥሁ ተውኋቸው። ሁኔታቸውንም ስመለከተው ከላይ እንደገለጽኩላችሁ በጣም የሚያሳዝን ነበር። ከዚያ በኋላ «በሉ አሁን ቀጠሮ አለብኝ» አልሁና አንድ ብር አውጥቼ ሰጥቻቸው በምትሔዱበት ጊዜ ሳይተይቁኝ እንዳትሔዱ አልኋቸውና እዚያ እንደ ፈሰሱ ትቻቸው ወደ መኪናዬ ገባሁ። ዘመዳችን የሆነችው ሴትዮም ነገሩን ሁሉ እንደሰማች «ልጆቼ በከንቱ ምን ያጉላላችኋል? ወደ ቤታችሁ ተመለሱና ተቀመጡ፤ እሱ እንደሆነ ዓለም በጄ ናት ብሏል፤ የእኅት የወንድምን ጉዳይት የሚመለከትበት አእምሮው ጠፍቷል» ብላ ላንዷ እኅቴ አንድ ውራጅ መሳይ ቀሚስ ላንዷ ነጠላ፤ ለወንድሜ የልጅዋን አሮጌ ኮት ለመሣፈሪያም የተቻላትን ያህል ረድታ ቤቴን ታውቀው ስለ ነበር ልጆቹን ይዛ ወደ ቤቴ መጣችና ከበር ሁና ልጅ ላከች። እኔም ኃይለኝነቷን የማውቅ ከመሆኔ በላይ በከተማ ውስጥ አሉን ከምላቸው ዘመዶች አንደኛዋ እሷ በመሆኗ ጥቂት ደቂቃዎች ሳልቆይ ወጥቼ ተገናኘኋት። ልጆችን አስከትላ መምጣቷን ባየሁ ጊዜ ለጠብ እንደመጣች አወቅሁና ከው ብዬ ደነገጥሁ። እሷም ሰላምታ ከመስጠቷ በፊት «የኛ ዘመናይ አንተን ፍለጋ ብለው መጥተው በሜዳ ፈሰው ይቅሩ?! ባይሆን መሣፈሪያ አትፈልግላቸውም? የናት የአባታቸውን ሀብት ስብስብ አድርገህ ለራስህ ይዘህ እንደ አሻንጉሊት ትጫወትባቸዋለህ፤ ሰው ከናት ከአባት ልጅ የሚቀርበው ዘመድ እንዴት ሊኖረው ይችላል? ሞልቶህ ተርፎህ ከዚህም በቀር የነሱን

ሀብት ሁሉ ሰብስበህ ይዘህ የነሱን ዝምድና እንደዚህ መጥላትህ በምን ምክንያት ነው። እንዲያውም ርስታቸውንም ሀብታቸውንም አካፍላቸው እያለች ይህንንና ይህን የመሰለውን እውነተኛ ቃል ተዘምዶ በቀሰቀሰው ደም ፍላት ስትናገረኝ ልጆች አንገታቸውን ደፍተው ያለቅሱ ነበር። ዘመዳችንም የምትናገረው ጠፍቷትና ልጆችን ስታይ ዕንባዋ ተናንቋት ዕንባዋን እየጠረገች «አዬ ሞት እግዚአሔር ይይልህ! የማናህሎሽ ልጆች እንዲህ ሆነው ለማየት ያበቃኸኝ!» በማለት መሪር ኃዘኗን ትወረውርብኝ ነበር። በእውነቱ በዚህ ጊዜስ እኔም በጣም ተጨንቄ ነበር የሆነው ሆኖ ማልቀስ ይቅርና ግንባሬን እንኳ አላላበኝም። ወዲያው በስንት ምጥ ሠላሳ ያህል ብር አወጣሁና «አንቺ ይህንን እንደሚሆን አድርገሽ ላኪያቸው፤ እኔ ምን ላድርግ ብለሽ ነው ነገሩን እያወቅሽ! ችግር ሆነብኝ እኮ! እንግዲያ ለናቴ ልጆች መቼ ይህን ያህል እሆን ነበር» አልኳት። እሷም መለሰችና «እባክህ አላማረብህም ዝም በል ምኑ ነው የቸገረህ? አውቅሃለሁ ገንዘብ ሞልቶሃል የጋራ ሀብታችሁ በእጅህ ነው ያለው እንዲያው ቀጥቃጣ የማላውቅበት ሐሳበ ቢስ የእኅት ወንድም መከራ የሚያሳዝነኝ ነኝ አትልም» አለችኝ። እኔም መለስሁና «በይ ተይው እቴ እኔን ይስጥሽ እንዳልልሽ እንዲደርስብሽ አልፈልግም» ብዬ ስመልስላት ወዲያው ቀበል አደረገችና» ደግሞም እኮ ይኸ ሁሉ መንገብገብ ደስ ብሎህ ላትኖር ነው ይብላኝልህ ታሳዝነኛለህ!! በል ደህና ሁን» ብላ እኅቶቼንና ወንድሜን አስከትላ እየተሸቀነጠረች ተጓዘች እነሱም ዕንባቸውን እያዝረከረኩ ተመለሱ። ለምን አያልቅሱ? ለምን ግራ አይግባቸው? የሕይወታቸው ጋሻና መከታ አድርገው በተስፋ ሲጠብቁኝ የኖሩ እኔን አይደለምን? በዕድሜአቸው አነስ ያሉት ያስተምረናል ያደረጉት አስተናባሪ በማጣት የደረሰብንን ጥቃትና ችግር አስወግዶ በደኅና ያኖረናል ብለው የተማመኑት እኔን አልነበረምን? ሌሎችስ ቢያጠፉ ለጥፋታቸው ይቅርታ የሚያስደርግላቸው አንዳንድ ምክንያት አላቸው። አንዳንዶቹ ዕውቀትና ቅን አስተያየት እያላቸው ገንዘብ ስለሚቸግራቸው ሊያደርጉት የሚገባቸውን ሳይሠሩ ይቀራሉ። አንዳንዶቹም ገንዘብ እያላቸው ዕውቀትና ቅን ሃሳብ ስለሌላቸው፤ ጉልበታቸውንና ገንዘባቸውን ለደግ ነገር ሳይሆን ለክፋት ያውሉታል። እኔ ግን ዕውቀት እንዳገኘ ተምሬ ገንዘብም ሞልቶኝ ሳለ ከሌሎች የከፋሁ ወንበዴ ሁኜ በመገኘቴ ሊታዘንብኝ ሊታዘልኝም ይገባል። እኔን ፍለጋ የመጡ እህቶቼና ወንድሞቼ ቤቴን ሳያዩ ምንም ሚስቴን ፈርቼ ነው። ግን ከዚች ወንበዴ ሚስት ተጠግቼ አንድኖር ምን አስገደደኝ? ያው የማልጠቀምበት ጥቅም መፈለጌ ነዋ! ጥቅም! ጥቅም! የግል ጥቅም! የተፈጠርሁም ለግል ጥቅም! የምኖረውም ለግል ጥቅም! የምሠቃየውም ለግል ጥቅም! ይህ ስስት ይለቀኝ ቢሆን አሁን ምናልባት ላንድ ቀን የሆዴ በሽታ ለቆኝ ከዚያም የብዙ መቶ ሺ ሰዎች የምግብ ፍላጐት አድሮብኝ በየቦታው ያለውን ምግብ ሁሉ አጓምቼ ባየሁት! ላንድ ሕይወቴ! በበሽታ ተጨንቆ ያንድ ድሀ ያህል ለመብላት እንኳ ላልቻለ ሕይወቴ! በሚስቴ ዘንድ እንኳ ክብር አግኝቼ ላልኖርሁበት ሕይወቴ ምኑ ነው ያባከነኝ? የመጽሐፍ

ቅዱስን ቃል ጥሼ «ሰይጣን የለም» ስል የለም ያልሁት ሰይጣን ይዞ ሲጋልበኝ ኑሮ ይሆን? በርግጥ ሰይጣን መርኖር አለበት። ሰይጣን ከሌለም የኔና የኔን የመሰሉት ሰዎች መንፈስ ሰይጣን ተብሎ መታመን አለበት። የኔ ዓይነቱ መንፈስ በሰው ላይ እንዳያድር በጸሎት መከላከልም ይገባል። ወደ ወሊሶ ሂጄ አባ ወልደ ትንሣኤ ቢያጠምቁኝ እስከ ዕለተ ሞቴ ተቆራኝቶኝ የቆየው የከንቱነት ሰይጣን ይለቀኝ ኑሮ ይሆን? ሳይለቀኝ አይቀርም ነበር ይሆናል። ግን ተቀድሜ አለሁ ያሁኑ ምኞቴ ሁሉ ከንቱ ነው። ግማሽ ሕይወቴ ወደ ሞት የተለወጠ ፍጡር ወደ ኑሮ ምኞት ገብቼ መማሰኔ ከንቱ ነው። ብቻ እንደኔ በሞት ወጥመድ ያልገባችሁት ተጠንቀቁ!

# ምዕራፍ ፰።

በተከታዩ በጋ በየመሬቴ የተዘመረውን የእህል ውጤትና ከብቶቼን ለማየት ወዳገር ቤት ሔድሁ። ወራቱ የበልግ ጊዜ እንደመሆኑ መጠን በመጋቢት ወር ላይ በጣለው ዝናም ሣሩና ቅጠሉ ለምልሞ ቁመው የነበሩት ምንጮች ሁሉ መውረድ ጀምረው ስለ ነበረ የአገር ቤት ትርእይት በጣም ደስ ይል ነበር። በከተማ ውስጥ የሰለቸኝን ብልጭልጭ ነገርና ግፊያ ሁሉ ትቼ ንጹሑንና የእግዚአብሔር የፈጠረው የተቀመጠውን የተፈጥሮ ውበት ሳይ ዓየሩም ስለቀለለኝ ልበላውና ልጠጣው አልችለው የነበረውን ነገር ሁሉ በደስታ መብላትና መጠጣት ጀመርሁ።

እነዚያ፤ እኔ በከተማው ቤቴ እንዲገቡ የማልፈልቅድላቸው ዘመዶቼ እኔን ስላዩ ለኔ መስተንግዶ በመጨነቅ የሚሆኑትን ያጡ ነበር። ሁኔታቸውን ላየ ሰው እኔን ለማስደሰት ሌላ ህነው ለመፈጠር እንኳ የሚፈልጉ ይመስሉ ነበር።

ለኔ ለከፉው፤ ለኔ ላውሬው ይህን ያህል የተጨነቁ ደግ ዘመድ ቢያገኙ እንዴት ሊሆኑለት ነው? ከቤታቸው ያገኙትን ነገር ሁሉ አሳምሮ ለማቅረብ ከሚያደርጉት ጭንቀት ሌላ፤ ገንዘብ እየተበደሩ ካቲካላና ሌላም የሚያውቁትን መልካም መስሎ የታያቸውን ሁሉ ለኔ ለመግዛት ሲጣደፉ ማየት ኅሊና ላለው ታላቅ አሳዛኝ ነገር ነበር። ለኔ ግን ሁሉም ከንቱ ነው። በማያዛልቅና ወሰን በሌለው የጥቅም ፍላጎት የታወረው ኅሊናዬ ለሰው መራራትን የሰውን ውለታ ማወቅንና እነዚህን የመሳሰሉትን አስፈላጊ ነገሮች ሁሉ ከዘነጋ ብዙ ዓመቶች አልፈዋል። ባገር ቤት ያሉ ቤተ ዘመዶቼ ዛሬ እንደማስታውሰው ብዙ ችግሮች ነብሩባቸው። የትምህርት እጦት፤ በሽታ የሹማምንት ጉጭጉጫ፤ የመሬት ጥበትና ይህን የመሰሉ ብዙ ጉጂ ነገሮች ነበሩባቸው። እነዚህን ችግሮች በሙሉ ለማስወገድ ጥቂት ጊዜ የሚጠይቅ ቢሆንም እንኳ እኔና እኔን የመሰሉት ተረዳድተን በመሥራት በቀላሉ

ልናስወግዳቸው የሚቻሉ ነበሩ። ግን አንዱንም አልነካኋት። ጥሩ ሰው ሁኖ ለመገኘት ያለፉትን መንቀፍ ሳይሆን ካለፉት የተሻለና በበለጠ ጠቃሚ የሆነ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል። ምናልባት እንደኔ ወደ ሀገር ቤት ወጣ እያሉ የሀገር ቤት ኗሪ የሆኑት ወገኖቻችን ባላቸው ዕውቀትና ዓቅም የሚፈጽሟቸውን በጎ ተግባሮችና ግዳጆች መመልከት ታላቅ ትምህርት ሊሰጥ ይቻላል። ከዚህም በቀር በአሁኑ ይዞታችን እኛ እነሱን ረዳን ከማለት ይልቅ በነሱ ጫንቃ ላይ ሁነን እንኖራለን እኛ በትምህርት ጐልምሰናል የምንል ሰዎች ከምንሰጠው አርአያነት ይልቅ እነሱ በወግና በባሕል ያገኙት መልካም አርአያነት ይበልጣል ብሎ ለመናገር የሚገደድበት ምክንያት ያጋጥመዋል።

ምን ጊዜም ቢሆን አንድ ሰው ከፍ ያለ ተግባር ሊፈጸም የሚችለው የግል ጥቅሙን ለጋራ ደስታና ጥቅም መሥዋዕት ለማድረግ በጐ ፈቃድ ሲኖረው ነው እንጂ በተአምር ሊሠራ የሚችልስ የእግዚአብሔር ቅዱስ ብቻ ነው።

የታላቅ ሥራ ውጤትን ለማግኘት ታላቅና አድካሚ የሆነውን የመሥዋዕትነት አቀበትና ቁልቁለት መውጣትና መውረድ ያስፈልጋል።

ሞሊዬር የተባለው የፈረንሳይ ጸሐፊ «እውነተኛ ወዳጅነት በእርግጥ አስፈላጊ በሆኑ ነገሮች ራሱን ገልጦ ማሳየት ይገባዋል» ብሎ ተናግሮ ነበር እንዲሁም ሌላ አንድ ጸሐፊ «አደራረጐች ከቃላት የበለጠ ይናገራሉ» ብሏል። የኔ አገሬን መውደድ የኔ ወገንን አፍሪቃነት የኔ ሙያና የኔ ችሎታ ግን በወግና በመምሰል ብቻ ሲገለጽ በእውነትና አስፈላጊ በሆነ ነገሮች ስላልተገለጸ ወሬዬም የነውሬ ማዳመቂያ ብቻ ሁኖ ቀረ እንጂ እኔንም ሆነ ሌሎችን ሊጠቅም አልቻለም። ይልቁንስ በአገር ቤት የሚኖሩት ወገኖቼ እኔን ያህል ያውቃሉ ሳይባሉ ከኔ የተሻለ ይሠራሉ። በመጀመሪያው እንደነገርኋችሁ ከአጐቴ ሚስት ተጣልቼ ስወጣ የወልጆቼ ጐረቤቶች ወይዘሮ ወላንሣና አቶ ውብነህ ከነልጆቻቸው ያሳዩኝ የማይረሣ ፍቅርና ርኅራኄ በሰብአዊ ስሜት ፍልስፍና የተራቀቀ ዕውቀት አለው የሚባል ሊቅ ሊያደርገው ከሚችለው በላይ የሆነ በይገባኛልና በምርምር የተደረገ ሳይሆን ከንጹሕ የተፈጥሮ ባሕርይ የመነጨ ነበር። እኔ ሳይቸግረኝ የነፈግኋቸው ከኔ የተለየ የኑሮ ሁኔታ ስላላቸው የተጸየፍኋቸውና የናቅኋቸው ቤተ ዘመዶቼ ለኔ ለክፉው ያደረጉት ልግሥናና ያሳዩኝ አክብሮት እንደኔ ያለውን አጭበርባሪ በኅሊናዊ ውርደት የሚያኰመሽሽ ነበር። እንግዲህ የኔ መማር ያስገኘው ትርፍ ምን ሊሆን ነው? መዝረፍ? ያልተማሩትስ መዝረፍ አቅቷቸው መቸ ቀሩ? ያውስ ከድፍረት ጋር እንጂ! ማጭበርበር? ያልተማሩትስ መቸ ማጭበርበር አቃታቸው? ኩራት? ኩራትማ እንዲያውም ደንቆሮዎችን የሚጋልብ ፈረሰኛ ነው። በጠቃሚ ሥራም ከኔ ይልቅ እነሱው ይሻላሉ። እኔ አሁንም የምኖረው የሥራዬን ሳይሆን የማስመሰሌን ዋጋ፤ በእጥፉ እያገኘሁ በሰው ጫንቃ ላይ ነው። መኃይምኑ ሠራተኛ ግን ከራሱም ተርፎ እኔን ይጦራል። ግን ምን ይሆናል? ይህን ሁሉ ቀደም ብዬ ከዚህ የሞት

አፋፍ ሳልደርስ ብገነዘበውና የዓለምን ከንቱነት ባምን ኑሮ «ዘርፎና አጭበብሮ መክበር» የተባለውን የድንቁርና ፕሮግራሜን ሰርዤ ሠርቶና ደክሞ ራስንና ወገንን ማሻሻል፤ ደስታንም ሆነ መከራን ከወገን ጋር መካፈል፤ ትምህርትንና ዕውቀትን እንዲሁም የድካምን ፍሬ ለሌሎች ማካፈል፤ እውነተኛ ሰው ሁኖ መገኘት በአዲስ ዘዴ አዲስ ኑሮና አዲስ መሻሻል መፍጠር በሚል አዲስ መንፈስ እመራ ነበር። ሌሎችን በዚህ መንገድ ለመስደድም እንደ ቅዱስ ጳውሎስ ድካምንና መከራን ሳልፈራ እሰብክ ነበር። ባለፈው ዘመኔ ግን «ማን ያሠራኛል?» የሚለውን ጋሻዬን ብቻ እየመከትሁ ከመኖር ብቻ የተሻለ ነገር አልሠራሁም። ብዙ የግል ሀብት ለማግኘት ስጣጣር ጥሩ ጥሩ መኪናዎች ጥሩ ጥሩ ቤቶች እንዲኖሩኝ ለማድረግ ስባክን የእኅቶቼንና የወንድሞቼን እንዲሁም የሌሎችን መሬት ስነጥቅ ማን እረዳት ነበረኝ? የሚገፋፋኝና የሚያደፋፍረኝ ያው የራሴ ፍላጐት ብቻ አልነበረምን? ሌላ ቅን ፍላጐት ቢኖረኝስ ደጋፊ እንኳ ባጣ ምን ተቃዋሚ ሊነሣብኝ ኑሯል? ፍላጐትስ ካለኝ ሥራዬና ድካሜ እንዴት ያለ ፍሬ ሊቀር ይችላል? ሚካኤል ፋራዴይ የተባለው እንግሊዛዊ ለታላቁ የኤሌክትሪክ ጥበብ አከናዋኝ ሊሆን የቻለው የዕለት ራቱን መጻሕፍት በመጠረዝ ሥራ እያገኘ አይደለምን? ቶማስ አልቫ ኤዲሰን የተባለው ፫ ወሮች ብቻ በትምህርት ቤት የቆየ አሜሪካዊ በኤሌክትሪክ ብርሃን የመጠቀምን የቴሌፎንን የተንቀሳቃሽ ስዕልን ድምፅን በሸክላ የማስተላለፍንና የሌሎችንም ብዙ ጥበቦች ያከናወነ በባቡር እየዞረ ጋዜጣ እየሸጠና በዚያው ላይ የጥበብ ፍለጋ ሥራውን እየተከታተለ አይደለምን? ዘርዝሬ ላልዘልቀው በትግል ብዙ የሠሩትን አዋቂዎች ስም መዘርዘሩን ልተወውና ባጭሩ ስናገር የሰውን ልጆች በግዙፍ ጥበብና በመንፈስ ጥበብ ከፍ ለማድረግ የቻሉት ብዙ ሰዎች እረዳት ቀርቶ ጥበባቸውንና የድካማቸውን ፍሬ የመግለጽ ነፃነት በሌላቸው ጊዜ እየተነሱ የሠሩ አይደሉምን? ፍላጐትን እንኳን እረዳት ማጣት ሥቃይና መከራ እንኳ አይገታውም። እኔ ግን ምንም ችግር ሳይኖርብኝ የመሥራት ፍላጐትም ሳይኖረኝ «መሥራት እፈልግ ነበር ግን የሚሠራኝ የለም። ብዙ ችግር አለብኝ» እል ነበር። ኧረ ለመሆኑ ይመርም ይክፋ አባቶቼ በበቅሎ እንደተቀመጡ ሊወስኑትና ሊቆርጡት ይችሉት የነበረው ትንሽ ነገር ብዙ ወራት እንዲፈጅ ከማድረግ እንኳ ሳልወጣ እንዴት ከሌሎች እሻላለሁ እላለሁ? በፊርማ አቅም እንኳ የሰውን ጊዜ የማባክንና ደጅ የማስጠና ሰው እንዴት በጐ ፈቃድና ዕውቀት አለኝ ልል እችላለሁ። ፊርማውን በጊዜው እንዳልፈርም የሚለከልለኝ አለ ብዬ ደግሞ ለመዋሸት እችል ይሆን? መቼም አንዴ ዋሾ ነኝ! መቼም አንዴ ተቃዋሚ አጥቻለሁ! እንዳሻኝ ልዋሽ። ሽክ! ያለችው ልብሴ! ዘናጯ መኪናዬ፤ ባንድንድ ነገሮች መካከል ጣልቃ እያገባሁ የኒውዮርክን ሰማይ ጠቀሶች፤ የለንደንን ስፋት፤ የፓሪስን ውበት፤ የጀርመንን ለምነት መናገሬ ቃሌን ሁሉ ላያሳምን ነወይ? በጊዜዬስ ታምኘበታለሁ። ችግሩ በግብሬ ከተወለዱባት መንደር ወጥተው ከማያውቁት ያገሬ ልጆች አንሼ መገኘቴ ነው። ያገሬ ጀግኖች በቆራጥነት እየተከላከሉ ነፃነታቸውንን፤ ያውም የሶስ ሺህ ዓመት ነፃነታችንን

አስረክበውናል። ያገሬ ሕዝቦች በምግብ በልብስ በመሣሪያ ራሳቸውን ችለው ኑረው አገራችንን አስረክበውናል። ያገራችን ሊቆች መንፈሳዊና ሥጋዊ ዕውቀቶችን ያለዋጋ እያስተማሩ ኢትዮጵያዊ ዕውቀት አስተላልፈውልናል። ጊዜው ሲፈቅድም የሌሎች ከፍተኛ ዕውቀት ወዳገራችን በሰፊው ገብቶአል፤ እኛም በሀገራችን ሕዝብ የላብ ፍሬ እየተረዳን ትምህርት አግኝተናል። ብዙዎች ወንድሞቼ እንደኔ የትምህርት ዕድል ያገኙት በተቻላቸው መጠን ሀገራቸውን ለማሻሻልና ያስተማራቸውን ሕዝብ ለማገልገል ሲጣጣሩ ይገኛሉ። እኔ ግን ትምህርቴን የንጥቂያ መሣሪያ አደረግሁት። የተለያዩትን አንድ ለማድረግ ምሳሌ መሆን ሲገባኝ ራሴን የተለየ ሰው በማድረግ የልዩነት መሥራች ሆንሁ። እኔ ለዓለም የማበረክተው አገልግሎት በጣም ትንሽ ሁኖ ሳለ በትንሿ አገልግሎቴ ስመካ ብዙ ለሚጥቅሙት ሰዎች ተቃዋሚ ሆንሁ። እንኳን እኔ ሰዎችን በጠፈር ላይ አዙረው የሚመልሱ አስደናቂ መሣሪያዎችን የሚሠሩ ሳይንቲስቶች እንኳ በዓለም ተግባር ላይ ያላቸው ድርሻ በጣም ትንሽ ነው። ከድንጋይ ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ሲነሡ የኖሩ ተመራማሪዎች ለሥራቸው መሠረት የሆነ ብዙ መረጃ ባያቆዩላቸው፤ ገበሬዎች፤ እህልን ዘርተውና ሰብስበው፤ ባለወፍጮዎች ፈጭተው ምግብ አብሳዮች አብስለው የዕለት ምግባቸውን ባያቀርቡላቸው። ልብስ ሠሪዎች ልብስን፤ ቤት ሠሪዎች ቤትን ባያዘጋጁላቸው እንደዚሁም ሌሎችን ለሕይወት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ሁሉ በየክፍሉ እየተዘጋጁ ባያገኟቸው ኑሮ ሳይንቲስቶች የጠፈር መርከብ ለመሠራት የሚደክሙበትንና የሚያስቡበትን ጊዜ ለዕለት ጉርስና ልብስ ሲባክኑ ባሳለፉት ነበር።

ነገር ግን የሠለጠነ ሕዝብ የተፈጥሮ ኃይልን በየመንገዱ ተሰልፎ ስለተዋጋውና የያንዳንዱን ሰው ዋጋ አውቆ ስላከበረ፤ ሁሉም በያለበት እየበረታ የጋራ ደስታና ታላቅነት በመካከል ተገኙ። እንደኔ ያለው ዋጋ ቢስ ግን ተገቢ ተግባሬንና የግሌ የሆነውን መጠነኛ ድርሻ እንኳ ሳላከናውን ዓለም በኔ መኖር ብቻ የምትሽከረከር ይመስለኝ ነበር።

የሰው ልጅ በዓለም ላይ ሊፈጽማቸው ከሚችላቸው ተግባሮች ሁሉ ይበልጥ ከፍተኛ የሆነው ከሰዎች ተስማምቶ መሥርቱና ዓቅሙን ለሰው ዘር አገልግሎት ማዋሉ ብቻ ነው። የሰው ዘር በዓለም ላይ መኖር ከጀመረ ብዙ ዘመናት አልፈዋል። ወደፊትም የሰው ዘር በዓለም ላይ ብዙ ጊዜ ሊኖር ይችል ይሆናል። (እንደኔ ያሉ በቃኝ አይሌዎች በኑክሊዬር ቦምብ ባያጠፉት)። ያንድ ሰው ዕድሜ ግን በጣም አጭር ነው። አንድ ሰው ባጭር ዕድሜው ውስጥ ብዙ ዘመን በዓለም ላይ ለኖረውና ወደ ፊትም የመኖር ተስፋ ላለው የሰው ዘር መልካም ሊሠራ ከቻለ ዓቅሙን መንፈግ መች ይገባው ነበር። በከተማ ውስጥ ከሠራኋቸው ብዙ ቤቶች አንዱን የገጠር ክሊኒክ ባደርገው ብዙ መኪና ከመቀያየር አንዱን ለአንዲት በክረምት ወራት ብዙ ባላገሮችን ለምታስቸግር፤ አንዳንድ ስዎችንም ለምትወስድ ወንዝ ድልድይ ባሠራበት፤ ለብቻዬ ዓቅም ቢያንሰኝ እንኳ ከሌሎች እንደኔ ብዙ ሀብት

ካላቸው ጋር ተረዳድቼ መልካም ነገር ብሠራበት ጥቅሙ የትና የት ነበር? ኧረ ስንቱ? ከያዝሁት አንድ አገር መሬት ለሌላው እንኳ ቢቀር እንደኔ ባለ ርስት ለነበሩት እኅቶቼና ወንድሞቼ ከፍዬ ሰጥቼ ከጢሰኝነትና የጉልበታቸውን ፍሬ አጋማሽ እንደኔ ላለ መሬት ነኝ ለሚል ጮሌ ከመገበር ባድናቸው ምን ነበር? ይህን ባለማድረጌ ምን አገኘሁ? ከሰው የበለጠ ደስታ አገኘሁበትን? ከድንገተኛ ሞት አመለጥሁን? የዕለት ምግቤን እንኳ በሚገባ እየተመገብኩ እስከ ጊዜው እንዳልቆይ በጉበትና በስኳር በሽታ ስሠቃይ ነው የኖርሁት። «ገንዘብ ለሚሠራበት መልካም ባሪያ ነው። ለእሚገዛለት ግን ክፉ ጌታ ነው» የተባለውን ጥቅስ በከንቱ ማለፌ በሕይወት ዘመኔ ከሠራሁት ስህተት ሁሉ የበለጠ ሁኖ አገኘሁት። በዚህ ሁሉ ምክንያት ተምሬ እንዳልተማርሁ ሁኼ በከንቱ ቀረሁ። ካልተማሩት ወገኖቼም አነሥሁ ግን ይህ ሁሉ አሁን ጊዜዬ ሲያልቅ እንጂ ያን ጊዜ አልተገነዘብሁትም።

# ምዕራፍ ፱።

ከፍ ብዬ ከገለጽሁላችሁ የአገር ቤት ጉብኝቴ በኋላ ወደዚያ ቀበሌ እንደገና ለመመለስ ዕድል አላገኘሁም። በመኖር ተስፋ የካብሁት ዕድሜዬ ሳላውቀው ወደ ማለቁ ተቃርቦ ኑሯል። ከነገ ዛሬ ይድናል እያልሁ የማስብለት ጤናዬም መንምኖና ተጠቅቶ ኑሯል። ዓላማ በሌለው ተስፋ ሳቅበዘበዘው የኖርሁት ሕይወቴም ከኔ ተላቆ ለመጨረሻው ታላቅ እንቅልፍ አረካክቦኝ ሊሔድ ጊዜው ደርሶ ኑሯል። ግን ለሞት እጅን እስኪያሲይዝ ድረስ አለሁ! እያለ የሚያሞኘው የመኖር ተስፋ ወደኔ የሚገሠግሠውን ሞትን ከልሎ አይዞህ አይዞህ ይለኝ ነበር።

እኅቶቼንና ወንድሞቼን ምንም ሳላደርግላቸው እነሱን በታላቅ እንግድነት ሳስጨንቃቸው ሰንብቼ ብቻ ወደ ከተማዬ ጉዞ ጀመርሁ። ጢሰኞቼን ስለሚቀጥለው የዘር ሁኔታ አነጋግሬ አዲስ አበባ አምጥተው ሳይሸጡ እዚያ በርካሽ በመጣላቸው ብገስጻቸውም ከህል ከቅቤና ከማር ሽያጭ የተገኘውን ጥሬ ገንዘብ ሰብስቤ መንገድ እንደጀመርሁ ወግ ነውና! ልማድ ነውና! ወንድሙ ተገኝቼ! እኅቶቼና ወንድሞቼ ሴቶችም ወፍጮአቸውን ወንዶችም እህል ውቂያቸውን ጥለው እስከ መኪና መንገድ የምደርስበትን በቅሎ እየሳቡ እኔን ከብብ አድርገው መሸኘት ጀመሩ። አዬ ጸጸቴ! አዬ መረገሜ! ዓይኔ ፈስስ ይበል! እሱስ ሊፈስ ነውና! ያቺ ትንሽ ሳለች ካጐቴ ቤት ስትንገላታ ትቻት ለትምህርት የሔድሁት! ያቺ ሥራ እንደጀመርሁ ወዳገር ቤት ስሔድ ጭርንቁስ ለብሳ እበት ስትጠፈጥፍ ያገኘኋት! ያቺ እኔን ለመጠየቅ መጥታ እቤቴ ሳላስገባት እያለቀሰች የተመለሰችው! ያቺ አሁንም ያላለፈላት ከልታማ! ያቺ ትንሿ እኅቴ አሁንም እንባዋን በሁለቱ ጉንጮቿ እያፈሰሰች ትሸኘኝ ነበር። እኔም፤ የወንድማችንም፤ የሷም በሚመጣው ክረምት መሞት በመንፈስ

ታይቷት ይሆን? ንሱሕ ናትና እንደኔ ወንጀለኛና ጨካኝ አይደለችምና! እንዲህ ሳያምርብን! ለባሰ መከራ ጠልን ባንድ ወራት ማለቃችን በመንፈስ ታይቷት ይሆናል። አዬ ማሚቴ! አዬ የናቴ ልጅ! ዘወትር ባይንሽ ውሀ ሞልቶ እያየሁሽ ዘወትር ተጐሳቁለሽና የልጅነት ሰውነትሽ አይመስሉ መስሎ እያየሁሽ! ካልቸገረኝ ነገር አንድ ቀን እንኳ ደስ ሳላሰኝሽ መሞትሽን ልስማ?! ብዙ ጊዜ ላልቆይ ቀድመሽኝ ለመሔድ ለምን ቸኮልሽ? ምነው እስከሞት ጠብቃችሁኝ ብትከተሉኝ ኑሮ! ቀድሜያችሁ የተወለድሁ እንኳ እኔ ነበርሁ። ሁሉን ነገር ቀድሜ የምነጥቃችሁ እንኳ እኔ ነበርሁ! ሞትን ቀድማችሁ ነጥቃችሁኝ? በበሽታዬና በጸጸቴ ብቻ እየተሰቃየሁ ብሞት?! ለወንጀሌ ቅጣት የበሽታና የጸጸት ሥቃይ አይበቃውምና በኀዘንም እያሰቃየነው ይሙት ብላችሁ ነው እንደዚህ ባለ በጭንቁ ጊዜ ላይ መርዶአችሁን ያስላካችሁብኝ? እንዳልወቅሳችሁ ግፍ ነው። እናንተ እንኳ ያን ያህል በድያችሁ ሳትጠሉኝና ሳትወቅሱኝ ሙታችኋል! የኔ በጎች!! የኔ ቂም የለሾች!! አዬ! አዬ ሰው መሆን! ይህ ርኅራሄ! ይህ በሰላም አላስሞትህ ያለኝ ጸጸት ምነው ቀደም ብሎ ቢሰማኝ? ወንድሜ! እኅት ዓለሜ! ገንዘቤ ሁሉ ለናንተ ቁርባንና ተዝካር እንዲሆን ብናዘዘውና የተዝካር ቁርባናችሁ ድግስ ቢደባለቅ ያለፈውን የመከራ ዘመናችሁን ይፍቀው ይሆን? ወይስ በመቃብራችሁ ላይ ታላላቅ የድንጋይ ቅርጽ ባስደርግላችሁ ስትሰቃዩ የኖራችሁበትን ጊዜ መልሶ የሰላምና የደስታ ጊዜ ያደርግላችሁ ይሆን?? ኧረ ውሸት ነው። ተዝካሩም ያንድ ቀን መሣከሪያ ሐውልቱም የቋሚ መደለያ ነው እንጂ ካለፈው የናንተ ጭንቅ ያንድ ቀኗን የእንጀራ እናት የራብ ቅጣት እንኳ እንደማይቀንስላቸው አውቃለሁ። አህ አዬ የኔ ሥቃይ ዓለም ለሁሉ የምትበቃ ሰፊ ስትሆን እኔ ጠባብና ጥርቃቅ አድርጌባችሁ እድነተሰቃያችሁ ኑራችሁ እንደተሰቃያችሁ ሞታችሁ? ምነው የተፈጥሮ ሦስት ጊዜ ሙቼ የናንተን የአንዳንድ ቀን ሞት ባስለወጥሁት! እህ! እህ! እህህ! አዬ ጸጸቴ! ምነው አሁን ያመለጠን የምትፈሰው እንባዬ ቀደም ብለህ ያይኔን መሐል እንኳ ብታረጥብልኝ ኑሮ!! ሰዎች ይቅርታ አርጉልኝ አሳዛኙና አእምሮዬን ይዞ ሌላ ነገር አላስገባም ያልወ ስሜቴ እየጠለፈ የነገሩን ተራ አሳሳተብኝ።

ይኸውላችሁ ካገር ቤት ተመልሼ በጋዋን በደኅና ጨርሼ ከክረምቱ አጋማሽ ላይ ከዚህ ዓለም ጣጣ ለመገላገል ምክንያት የሆነኝ ይህ በሽታ ተቀስቅሶብኝ በጭንቅ ያዘኝ። ከዚያም ቶሎ ብዬ ወደዚህ ሆስፒታል መጣሁና በሐኪም ትእዛዝ በዚችው አሁን ባለሁባት ክፍል ተኛሁ። እዚህ በተኛሁ በሦስተኛው ቀን አንዱ ወንድሜ «ግማሹን ፍሬ ለባለ መሬቱ ሊሰጥ ወደ ተከራየው መሬት ሔዶ ዘር ሲዘራ ውሎ ማምሻ ሲመለስ በቤቱና በርሻው መካከል ያለችው ወንዝ ሞልታ እሻገራለሁ ሲል ካንዱ በሬው ጋር ወሰደችውና ሞተ» እንዲሁም ባሁኑ ሁኔታዬ ስሟን እንኳ ሳስታውሰው ዕንባዬ የሚጐርፍላት ትንሿ እኅቴ «በመከራ ባደገችበትና በኖረችበት ያጐታችሁ ቤት እንዳለች በመንደሩ የገባው የተስቦ

በሽታ ይዟት በወግ እንኳ ውሀ የሰጣት ሳይኖር ራሴን ባለች በ፫ኛው ቀን ሞተች። የቀሩትም ታመዋል እስኪ እግዜር ያውቅላቸዋል» የሚል መርዶ ደረሰኝ።

ይኸውላችሁ በሰላም እንዳልሞት ያደረገኝ ጩሀ! ጩሀ! አልቅስ! አልቅስ! የተወለድህበትን ቀን አርገም ያሰኘኝ መርዶ ይህ ነው።

መርዶውም አይደል! የሞት ቀላል ነው። ሞት የፍጡር ሁሉ ገንዘብ ነው። ሞትም በልዩ ልዩ መንገዶች መምጣቱን አውቃለሁ። እኔን ያስጨነቀኝ የመርዶው መርዶ ነው። እኅቴንና ወንድሜን እኔ የገደልኋቸው መሰለኝ እንጂ የተፈጥሮ መዘዝ የገደላቸው አልመስለኝም። የነሱን የደምና የመከራ ዋጋ እኔ እጠቀምበታለሁ አልል፤ ሳልደሰት ኑሬ እኔንም ሞት ከጁ በማላመልጥበት ሁኔታ ስልሞዬን አንቆ ይዞኛል። ተስፋዬ ተፈጸመ። ዓለም እኔን አታለለችኝ። ተጫወተችብኝ እስካሁን ብትበድሉኝም በብዙ ነገሮች ታባብለኝና ትደልለኝ ነበር። አሁን ግን ተመልሼ ታዘብሁሽ ልላት እንዳልችል ለመጨረሻው ወርውራ ገደል ጨምራኝ ሔደች። ሰው በዘዴና በብልጠት በውቀትና በሀብት ተደግፎ ሰው ከመሆን ግዳጁ ሊያልፍ እንደማይችልና ሁልጊዜም ሰው ራሱን እንደሚያታልል አስረዳችኝ። ዓለም እኔን ከከዳችኝና ሕይወቴን ለሞት ካስረከበች በኋላ ከሕይወቴ ጋር የነበረውን ከንቱነት ከኔ ሕይወት ገፋ ሌላውን ልታጭበረበብርበት ስትወስድ ታየችኝ። እኔም በዚህ ኑዛዜ ልቃወማትና ሌሎችን ላስጠነቅቅ ፈለግሁ። በትምህርቴ እስከ ዛሬ ድረስ ደኅና ነገር አልሠራሁም ነበር። ነገር ግን የትምህርት ዋጋው ይህ ነው! አሁን በመጨረሻ የተሻለኝን ያህል ሠራሁበት። ለማይረባው ከንቱ ስሜ ሳልጠነቀቅ ራሴን መማሪያ እንዲሆን አቀረብሁት። ወንጀሌን ነውሬን ጸጸቴን፤ ኀዘኔን፤ ገመናዬን በሙሉ ዘርግፌ ባለችኝ ጥቂት ጊዜ ገለጽሁት። በኔ መማር የቋሚዎች ፈንታ ነው። እንግዲህ እኔ ከዓለም የምካፈላችሁ ነገር አንዲት ቅንጣት መሬት ብቻ ናት። እሷንም ቢሆን ውስጧን እንጂ ላይዋን እንዳሻችሁ አድርጓት። በላዬ ላይ ጨፈራችሁ ይህን አደረጋችሁብኝ ለማለትም መብት የለኝም። ለናንተ ጠቃሚያችሁ ከሆነ ከነዚሁም ከልክሉኝ። እንደ ሰዱቃውያንም ሬሣዬን አቃጥላችሁ አመዱን በትናችሁ የመሬት ስስት በያዛቸው ግብዞች አየተገፉ መድረሻ ላጡት ወገኖቼ የመቃብሬን መሬትም ጨምራችሁ ስጡልኝ። መሬትን ገበሬዎች ይጠቀሙባት እንጂ። ሠራተኞኖች ያስጊጡና ያለምልሟት እንጂ! የረኀብና የብርድ የሌላም ችግር ማስወገጃ የሆኑ ፍሬዎችን ያስወልዷት እንጂ ሙታኖች ተከናንበናት ለምን እንተኛ? እኔስ ምን ጊዜም ሙት ነኝ። ሕያው በምባልበትና ሙዋች በምባልበት ዘመን ያለኝ ልዩነት በጣም ትንሽ ነው። በሕይወት ሳለሁ አፌ የማይረቡና ዋጋ ቢስ ነገሮችን ይዘባርቅ ነበር። እበላ እጠጣ እቀማ ነበር። ስሞት የቀሩብኝ ሥራዎችም እነዚህ ናቸው። ይልቁንም በሞቴ ታላቅ ተግባሮችን እንደምፈጽም ተስፋ አለኝ። ለፍላፊው አንደበቴ ታላቁን የዝምታ ግርማ ይጐናጸፋል። ንጥቂያና ማጭበርበርን የሚያህለው ወንጀሌ

ይወገዳል። ዓለም እጅግ ከብዷት የነበረው መጥፎ ሥራዬ ተወግዶላት የሚያስቀይማትን ሬሣዬን ብቻ ተሸክማ ትቀመጣለች። የድሮው ገብጋባ፤ ከወረቀት የተሠራ ኖት፤ ከብርና ከመዳብ የተሠራ ቤሣ ከጄ ሲወጣ የልቤ ሥር እንደ ተወጋ ስሸማቀቅና መፈጠሬን ስጠላ ያየችኝ ዓለም ሰውነቴን ለምስጦችና ለሌሎችም ልጆችዋ ስትመግበው ዝም ብዬ ስታየት ምን ትል ይሆን? የሚገርመኝ እኔን ነው እንጂ ለሷማ ምን አዲስ ነገር አለባት? ምኑስ ይገርማታል? እነ እስክንድርንና እነናፖሊዎንን እነ ሂትለርን የመሰሉትን ዓለምን በጃችን እናደርጋታለን ብለው ሲባክኑ የኖሩ የጦር ጣኦቶች፤ እነ ጳውሎስን፤ እነ ሞሐመድን እነ ቡድሐንና ሌሎችንም የሃይማኖት አርበኞች እነ ሶክራትስንና ፕላቶን የመሰሉትን ፈላስፎች እነ አልበርት አንስታይንን እነ አልክሳንደር ፍሌሚንግን የመሰሉትን ሳይንቲስቶች እነ ዊሊያም ሸክስፒየርን እነ ሌኦ ቶስልስቶይን የመሳሰሉትና ሌሎችን የተራቀቁ ደራሲዎች እነ ሊኦናርዶ ዳቪንቺን እነ ሚካኤል አንጀሎን የመሳሰሉትን የተራቀቁ ሰዓሊዎች እነ ማሕአተማ ጋንዲን እነ አብርሃም ሊንኮልንን የመሰሉትን የተባረኩ መሪዎች የበላች መሬት አይደለችምን? እኔን የመጨረሻው ታላቅ ዓላማዬ ወገኖቼን ነጥቄ የግል ሀብት በመሰብሰብ የኢትዮጵያ ሮኪፌለር መባል ብቻ የነበረውን እንስሳ ስትበላ ምን ይገርማታል? የሚገርማት አንድ ነገር ነው። ይኸውም ሰው እንደ መሆኔ መጠን ሞቴ ለቋሚዎች ወገኖቼ ኀዘን በመሆን ፈንታ ከሸክም ማረፍ ሲሆንላቸው ስታይ ነው። ባጭሩ በሞቴና በሕይወቴ መካከል ያለው ልዩነት ሞቴ ጠቃሚ ኑሮዬ ጐጂ ሆኖ መገኘቱ ነው።

የሕይወት ዘመኔን ሳይሆን የሞቴን ቀን እንድታስታውሱት ለኑዛዜዬም ደኅና ግምት እንድትሰጡት በማመን የሚከተለውን አደራ ጥየባችኋለሁ።

፩ኛ/ ሀብቴን ሁሉ ከሚስቴ እኩል ተካፍላችሁ ግማሹን ከሞት ለተረፉት እኅቶቼና ወንድሞቼ ስጡልኝ። ደግሞም ከመካከላቸው አንዱ አንደኔ ያለ ጮሌ ተነሥቶ እንዳይነጥቃቸው እናንተ እኩል አካፍላችሁ ስጡልኝ

፪ኛ/ የሀብቴን አጋማሽ እንደገና ከሁለት ከፍላችሁ እኩሉን ወላጆቻቸው ለሞቱባቸው ሕፃናት፤ ድሆች የሆኑትን የሚያሳድግ ሀብት ያላቸውን ሀብታቸውን በጥብቅና የሚጠብቅ ድርጅት መሥርቱልኝ።

፫ኛ/ ከዚህ በቀረው ካገር ቤት ኗሪዎች ጋር እየተረዳዳ የመሠረተ ትምህርት ቤት፤ የገጠር ክሊኒክ ያስቸጋሪ ወንዞች ድልድይ የሚሠራ የኑሮ ማሻሻያ ዘዴ የሚያስተምር፥ ድርጅት አቋቁሙልኝ። አደራ! ዕድሜን ስለሰጣችሁ የመጸጸቻ ጊዜስላደላችሁ አምላክ ብላችሁ ልመናዬን ፈጽሙልኝ። ሚስቴም አደራሽን ከድርሻሽ አልፈሽ አትበጥብጪ። አንቺም እኔን ተከትለሽ ባላሰብሺው ቀን መሔድሽን አትርሺ። ለብዙ ሀብት ብሎ የማይገባ ተግባር ሁሉ መፈጸም ምንም ትርፍ እንደማይሰጥ በኔ ተምረሻል። ተረድተሻል።

# የመጨረሻ ትንፋሼ።

አንድ አውሮፓዊ ደራሲ «የሞት መጥፎነቱ የሚዋደዱ ሰዎችን መለየቱ ነው እንጂ ሞት ራሱ ክፉ ነገር አይደለም» እንዳለው የኔም የወላጆቼም የዘመዶቼም ሞት ክፉ አይደለም። ሞትን ክፉ ነው የምልባቸው ምክያቶች፤ አንደኛ እንደኔ እኅቶችና ወንድሞች ያሉ ሕፃናትን እናት አባቶቻቸውን ገድሎ የዕድሜ ልክ መከረኞች ማድረጉ ፪ኛ እንደኔ ያለውን ሰው ለጸጸት ሳያበቃ በድንገት መግደሉ፤ ሶስተኛ እንደ እኔ እኅቶችና ወንድሞች በሥቃይ ዕድሜአቸውን ያሳለፉ ሰዎችንም ከሌሎች አስቀድሞ መግደሉ ናቸው።

ከሞት የሚከፋው የመኖር ተስፋ ነው። ሰው ሞትን ቢወደውና ከሞት የማይቀር መሆኑን ዘወትር ቢያስታውሰው በሕይወት ዘመኑ ሁሉ በቅንነት የተመሠረቱ በጐ ተግባሮችን ሳይሠራ ባላለፋቸው ነበር። ነገር ግን ምንም እንኳ ሟቾች መሆናቸውን ብናውቅ የመኖር ተስፋችን ከሞት ይልቅ ኑሮን ስለሚያስታውሰን ከደግነት ወደክፋት ስናጋድል እንገኛለን። የተማርሁት ትምህርት ሁሉ ቅን መንገድን አስረድቶኝ ነበር። እኔ ግን ከተማርሁት በጐ ነገር ይልቅ ማንም እንድከተለው ያላስተማረኝን ክፉ ሥራ እከተል ነበር። የኔው ዕድል አልፏል። በሕወት ያለችሁ ወንድሞቼና ወገኖች በኔ ተማሩ! በኔ ተመከሩ። እብቅንነትና በሚገባ ሁኔታ መኖር በሕይወትም ሆነ በሞት ጸጥታን የሚሰጥ እምሆንኑ ዕወቁ! ደስታን መፈለጋችን ወንጀል አልነበረም። ግን ደስታችን በሌሎች መከራ ላይ የተመሠረተ ከሆነ ደስታችንን ቀንሰን የመሰሎቻችንን መከራ ብናቃልል በጸጸት እየተቃጠሉ ከመሞት ያድነናል። ባለችን ትንሽ ጊዜም ሰላምን ለማግኘት ይረዳናል። እኔ የሰበሰብሁትን ሁሉ ሀብት ታውቁታላችሁ። ሠርቼ፥ የሰበሰብሁት ቢሆን ምንም ጸጸት አልነበረብኝ። ነገር ግን ይህን ሀብት ለማግኘት የእኅቶቼንና የወንድሞቼን ድርሻ ነጥቄ አንዱ ወንድሜ ያበቀለውን እህል እኩል ሊሰጥ ወደ ተከራየው የርሻ መሬት ሲሄድ በውሃ ሙላት መወሰዱ፤ በድኅነት የኖረችው እኅቴ በትንሽ በሽታ የሐኪም እርዳታ ሳታገኝ መሞቷ፤ ከዚህም በላይ በዓለም ላይ የኖሩባት ጥቂት ጊዜ በኔ ምክንያት ለነሱ መራራና አሠቃቂ ሁና መቆየቷ፤ እደሰትበታለሁ ብዬ የሰበሰብሁት ሀብት ተጨማሪ የህብት ምንጭ ትሆነኛለች ብዬ በተጠጋኋት የጥቅም ሚስት ምክንያት ሳልደሰትባት በመቅረቱ እንደ ኢዮብ የተወለድሁበትን ቀን ረገምሁ። ወደዚህ ዓለም የመምጣት ፍቺ እንደኔ ሁኖ ለማለፍ ከሆነ የሰው መፈጠር ርጉም ይሁን ሰውነቴ ዛለብኝ ከዚህ ብርቱ በሽታየ ላይ ህይ ብስጭትና ጸጸት ተደርቦ በጣም አደከመኝ! አሁንስ ሞት አጥብቆ ቀረበኝ በሰል። የጸጸቴ ስሜት እየደከመ ሄደ። የልቅሶዬ አደባባይ ታዬኝ። ሬሣዬን የያዘው መኪና ባበባ ጉንጉኖች አጊጦ በጸጥታ ሲጓዝ በብዙ መኪናዎችና በእግረኞችም ታጅቦ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲሄድ ታየኝ። አዬ ወግ! አዬ ልማድ! ደግ፤ ጀግና፤ ቸር፤ አዋቂ እየተባልሁ የልቅሶው ግጥም ሲደረደርልኝ፤


ወንድማችሁ ሞተ ተብሎ ሳጠቃቸው ለኖርሁት ዘመዶቼ መርዶ ሲላክልኝ ታየኝ። አዬ የሰው ሥራ! ከሰላምና ከጸጥታ አርቃኝ የኖረችው ሚስቴም እንባ ስታፈስልኝና ደረቷን ስትመታልኝ ታየችኝ። አዬ ባሕል! አዬ እምነት! እንደኔ ያለውን ሽፍታ ከፈጣሪ ጋር ለማስታረቅ በከበሮና በጸናጽል ካህናቱ ፍትሐቱን አደባለቁልኝ! የሀብታሙ ፍትሐት የጉዞው ፍትሐት ወረደልኝ። ከዕለት እስከ አርባ ከዚያም እስከተዝካር ይቆረብልኛል። ዋ! ልማድ በሕይወት ሲዘርፉት ከኖሩት ገንዘብ ሲሞቱ ቀንሶ መስጠት ቅን ሥራ ይሆን? አሁንማ ምን ማድረግ እችላለሁ? ራሴስ ለመሬት ልስጥ አይደል? ታላቅ የድንጋይ ቅርጽም በላዬ ላይ ይከመርብኛል። ክፉቴ ትዝ ብሏቸው ተመልሼ እንዳልወጣ፤ ወይም በሙታን ትንሣኤ ጊዜ እንዳልነሳ በኃይል መድፈናቸው እንደሆነ እንጂ ሐውልት የሚሠራልኝ ለየትኛው መልካም ሥራዬ መታሰቢያ እንዲሆን ነው? ወይስ ሬሣዬ ድንጋይ ተሸክሞ በሕይወቴ ስበድላቸው የኖርሁትን ሰዎች ይቅርታ እንድጠይቅ ብለው ይሆን? የኔ መሞት ባንዳንድ በኩል ያስደስተኛል ለሀገሬ ታላቅ ቀንበር በቶሎ እንደወደቅላት ሳስብ ጥቂት ተስፋ ይሰጠኛል። ግን ዕዳዬን ሳልከፍል በመሞቴ ያጸጽተኛል። እንደገና የመወለድ ዕድል ቢኖረኝ እንዴት ያለሁ ደግ ሰው በሆንሁ ነበር። ለዚች ዕድሜ፤ ለዚች ጥቂት ቀን እሷውን ደስታ ላላገኘሁባት ስንቱን ጭካኔና ክፋት ፈጸምሁ? በሉ ደኅና ሁኑ ልብ ይስጣችሁ። የልቤ ምት ሊቆም ጥቂት ደቂቃዎች የቀሩ ይመስለኛል! አዬ አምላኬ ለዚህ ዕድል ለምን ፈጠርኸኝ?

ከፈጠርኸኝስ ለሰዎች መከራ ምክንያት ሳልሆን በሕፃንነቴ ወራት በገደልኸኝ!!

ካደግሁስ ምነው ደኅና ሰው ባደረኸኝ ነበር!! የመኖሬ ታሪክ አለቀ! ይኸው የልቤ ምት ቆመ!

ምስጋና።

የዚህንና የሌሎች ብዙ መጽሐፎቼን የሽፋን ስዕል በነፃ እየሠሩ ለሠጡኝ ለአቶ አሥራት ወልደ መድኅን ያለኝን ልባዊ ምስጋና እገልጻለሁ። አ.ጉ.



# ስለደራሲው በጥቂቱ

አቤ ጉበኛ (፲፱፻፳፭ ዓ/ም በባሕር-ዳር አካባቢ፣ ይስማላ ጎጃም ተወልደው - ፲፱፻፸፪ ዓ/ም አዲስ አበባ ላይ አረፉ። ባለቅኔ፤ ደራሲና ገጣሚ የነበሩት አቤ ጉበኛ በስድስት ዓመት ፊደል ቆጥረው ንባብ ከተማሩ በኋላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ሲከታተሉ ቆዩ። ከዚያም ወደ ደንጎላ ሄደው በቢትወደድ መንገሻ ጀምበሬ ትምህርት ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀው ወደ አዲስ አበባ በመምጣት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀዋል።

አቤ ጉበኛ የመጀመሪያ ሥራቸው በማስታወቂያ ሚኒስቴር ሲሆን ቀጥሎም በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተቀጥረው በመንግሥት ሥራ ለስድስት ዓመታት ያህል ካገለገሉ በኋላ ሕይወታቸውን በአብዛኛው የገፉት በደራሲነት ነው። በ1967 እ.ኤ.አ. በአዮዋ ክፍለ-ሀገር ወደ ዓለም አቀፍ የጽሑፍ ህብረት ፕሮግራም (International Writing Fellowship Program) ሄዱ።

## የደራሲው ሥራዎች፦

1. መስኮት **(ግጥምና ቅኔ)**
2. እሬትና ማር **(ግጥምና ቅኔ)**
3. ከልታማዋ እኅቴ **(ልብ-ወለድ)**
4. ምልክዐም ሰይፈ ነበልባል **(ልብ-ወለድ)**
5. አንድ ለናቱ **(ታሪካዊ ልብ-ወለድ)**
6. የረገፉ አበቦች **(ልብ-ወለድ)**
7. ከመሰፍት ሠራዊት፥ ይጠንቀቅ ሰውነት **(ተውኔት)**
8. ቂመኛው ባሕታዊ **(ተውኔት)**
9. የሮም አወዳደቅ **(ተውኔት)**

10. የራሔል ዕንባ **(ተውኔት)**
11. የደካሞች ወጥመድ **(ተውኔት)**
12. አልወለድም (፲፱፻፶፫ ዓ.ም.) **(ልብ-ወለድ)**
13. የዓመፅ ኑዛዜ (፲፱፻፶፫ ዓ.ም.) **(ልብ-ወለድ)**
14. መሬት የማን ነው
15. The Savage Girl 1964 እ.ኤ.አ. **(በእንግሊዝኛ)**
16. Defiance 1975 እ.ኤ.አ. **(በእንግሊ**

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY